ትምህርት ዘጠኝ

1ኛ ቀን፡- ኢሳይያስ 12-23

1ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ብዙ ክርስቲያኖች ሌላ መንግሥት የተነሣባቸው በሚመስላቸው ጊዜ ወይም ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ጦርነት በሚካሄድበት ወቅት ተስፋ የሚቈርጡት ለምንድን ነው? ለ) ክርስቲያን እንዲህ ባሉ ወቅቶች ከተስፋ መቍረጥ ነፃ ይሆንና ይበረታታ ዘንድ ስለ እግዚአብሔር ማስታወስ ያለበት እውነቶች ምን ይመስሉሃል?

ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፥ ብዙ የተዛቡ ፍርዶችን በምድር ላይ ደጋግመን በምንመለከትበት ወቅት እነዚህን ሁኔታዎች ሁሉ በእርግጥ እግዚአብሔር እየተቈጣጠረ ነውን? በማለት እንጠይቅ። ምንም የማያውቁ ሰላማዊ ሕዝቦች ከጦር መኮንኖች ይልቅ የሚሠቃዩባቸው ጦርነቶች አሉ። እነዚህ ጦርነቶች ትክክለኞችና ፍትሐዊ አይደሉም። በአንድ ሕዝብ ላይ የሚደርሱና ሌላውን ሕዝብ የማይነኩ የሚመስሉ ድርቅና ራብ ወይም ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች በምድር ላይ ይታያሉ። የበለጠ ክፉና ኃጢአተኞች የሆኑ ሕዝቦች ከፍርድ እያመለጡ፥ በሌሎች ሕዝቦች ላይ ግን እጅግ ብዙ ችግር የሚደርስ በሚመስልበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚፈጸሙ ድርጊቶችን በእርግጥ እየተቈጣጠረ ይሆንን!? በማለት በትዝብት ሳንጠይቅ አንቀርም።

የእስራኤል ሕዝብም በተመሳሳይ ሁኔታ አጠያያቂ እንደሆነባቸው ጥርጥር የለውም። የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ ነበሩ። እግዚአብሔር በዓለም ላይ ካለ ከማንኛውም ሕዝብ ይልቅ ታላቅ እንደሆነ ያውቃሉ። ይሁን እንጂ እስራኤል ያለማቋረጥ በሌሎች ሕዝቦች ጥቃት እየደረሰባት ትሸነፍ ነበር። ይህ የሆነው እግዚአብሔር ደካማና ሌሎችን ሕዝቦች ለመቈጣጠር የማይችል ስለሆነ ነውን? እግዚአብሔር ከአሕዛብ አማልክት ይልቅ ደካማ ነውን? እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እንደሚፈርድ ተናግሯል። ይሁዳ ግን በሥነ- ምግባር ረገድ ከሌሎች አሕዛብ እጅግ የተሻለች ነበረች። እግዚአብሔር ታዲያ በይሁዳ ላይ የሚፈርደውና በሌሎች ሕዝቦች ላይ የማይፈርደው ለምንድን ነው? ኢሳይያስ እነዚህን ትንቢቶች በሚናገርበት ጊዜ በእርሱና እግዚአብሔርን በሚፈሩ ሌሎች

አይሁድ አእምሮ ውስጥ እነዚህና ሌሎች ጥያቄዎች ተፈጥረው እንደነበር ጥርጥር የለውም።

እግዚአብሔር ጥያቄዎቻቸውን በጸጋ ተቀብሎ አስተናገደ። እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል የተፈጸሙትን ድርጊቶች እየተቈጣጠረ መሆኑን በኢሳይያስ በኩል ለአይሁድ አሳየ። አሕዛብንም በአይሁድ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ሳይሆን፥ በራሱ ጊዜ በኃጢአታቸውና በክፋታቸው ይፈርድባቸዋል።

እግዚአብሔር በግለሰቦች ላይ በሕይወት አኗኗራቸው መሠረት እንደሚፈርድባቸው ብቻ ሳይሆን፥ መንግሥታትም በአጠቃላይ ቅን ፍርድን በማጒደልና የተለዩ ዜጎችን በመንከባከብ ስለፈጸሙት ድርጊት እንደሚፈርድ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። በተለይ የሚፈርድባቸው የራሱ ሕዝብ በሆኑት በአይሁድ ላይ በፈጸሙት ድርጊት ምክንያት ነው። አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነትና ለሕዝባቸው የሚሆነውን የሥነ- ምግባር መሠረት የተዉ አገሮችን ካሉበት ሥልጣን ፈጥኖ ያወርዳቸዋል። በሌላ ጊዜ ይህ ፍርድ በመቶ የሚቈጠሩ ዓመታትን ሊወስድና በክርስቲያኖች የሕይወት ዘመን የማይታይ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር በግለሰቦች ላይ ብቻ ሳይሆን፥ በመንግሥታትም ላይ እንደሚፈርድ እርግጠኞች ነን (ለምሳሌ ኢዩኤል 3)።

2ኛ ጥያቄ፥ መንግሥታትና መሪዎች ራሳቸውን እንዴት እንደሚመሩ፥ ሕግጋታቸው ምን ያህል ትክክለኞች እንደሆኑና ከመጽሐፍ ቅዱስ የሥነ-ምግባር መመሪያዎች ጋር እንዴት እንደሚስማሙና በእግዚአብሔር ፊት መልስ እንደሚሰጡ ማወቃቸው ለምን ይጠቅማል?

ዛሬ የምናጠናው በይበልጥ እግዚአብሔር በሕዝቦች ላይ እንደሚፈርድ የሚያሳየውን የትንቢተ ኢሳይያስን ክፍል ነው። እነዚህ ሕዝቦች በኢሳይያስ ዘመን ገናና የነበሩ ናቸው። ስለ እግዚአብሔር የተነገሩት እነዚህ ትንቢቶች ስለተፈጸሙ፥ ዛሬ ከእነዚህ ሕዝቦች አብዛኛዎቹ ሙሉ በሙሉ ጠፍተዋል።

3ኛ ጥያቄ፥ ኢሳይያስ 13-23 አንብብ። በእነዚህ ምዕራፎች የተጠቀሱትን ልዩ ልዩ መንግሥታትና እግዚአብሔር የወሰናቸውን ፍርዶች ዘርዝር።

1. በባቢሎን ላይ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 13-14፡1-23)

የመጀመሪያው ትንቢት የተነገረበት ሕዝብ የባቢሎን ሕዝብ ነው። ይህ ትንቢት በተነገረበት ወቅት ዓለምን ይገዛ የነበረው ታላቁ የአሦር የንጉሥ ነገሥት ግዛት ውስጥ ከነበሩት ዋና ዋና ከተሞች አንድዋ ባቢሎን ነበረች፤ ስለዚህ በአንድ በኩል፥ በባቢሎን ላይ የተነገረው ትንቢት በአሦር መንግሥት ላይ የተነገረ ነበር። ትኩረቱ በባቢሎን ላይ ስለሆነ ከዚህም የላቀ ትርጒም አለው። በኢሳይያስ ዘመን የነበረው ዓለምን የሚገዛ ዋና መንግሥት አሦር ሆኖ ሳለ ትንቢቱ በባቢሎን ላይ መነገሩ የሚያስደንቅ ነው። እግዚአብሔር ግን ከ150 ዓመታት በኋላ የይሁዳን ሕዝብ በምርኮ የሚያግዘው የባቢሎን መንግሥት እንደሆነ ያውቅ ነበር። ባቢሎን ርእሰ -ከተማ ከመሆኗ በፊት እንኳ እግዚአብሔር ስለ ጥፋቷ ተናግሮ ነበር። ባቢሎንን የሚደመስሰው የሜዶን መንግሥት እንደሆነም አስቀድሞ ተናገረ።

ኢሳይያስ 14፡12-15 በምሁራን መካከል ከፍተኛ ውዝግብን ያስነሣ ክፍል ነው። ይህ ክፍል ማንን ነው የሚያመለክተው? የባቢሎንን ንጉሥ ብቻ ነው ወይስ ሰይጣንንም ጭምር?

ይህ ክፍል በመጀመሪያ የተጻፈው በሕዝብ ዘንድ እንደ አምላክ ይታይ ስለነበረው ስለ ባቢሎን ንጉሥ ሳይሆን አይቀርም። ይሁን እንጂ ይህ ክፍል በብዙ መንገድ ሰብአዊ ንጉሥን ብቻ የሚያመለክት አይመስልም። ስለ አንድ ልዩ ሕያው ፍጡር የሚያመለክት ይመስላል። በዘመናት ሁሉ የኖሩ ክርስቲያኖች ይህ ክፍል የሚናገረው ስለ ሰይጣን ውድቀት ነው ብለው የሚያምኑት በዚህ ምክንያት ነው። ሰይጣን «የአጥቢያ ኮከብ» ወይም «ሉሲፈር» ተብሎአል። ይህ ክፍል ስለ ሰይጣን የሚናገር ከሆነ፥ ሰይጣንን ለውድቀት የዳረገው ትዕቢት እንደነበረ መመልከት እንችላለን። ሰይጣን እንደ እግዚአብሔር ለመሆንና በነገሮች ሁሉ ላይ ለመግዛት ፈለገ፤ ስለዚህ ከሰማይ ተጣለ። በራእይ 13፡4 እና 17፡3 ይህ ክፍል

በተምሳሌታዊነቱ በዘመናት መጨረሻ በሰይጣን ቊጥጥር ሥር ስለሚሠራው ክፉ መሪ ስለ አውሬው የተጠቀሰ ይመስላል።

4ኛ ጥያቄ፥ እነዚህ ጥቅሶች ትዕቢት በእግዚአብሔር አመለካከት ምን ያህል የከፋ ኃጢአት መሆኑን እንዴት ያሳያሉ?

ስለ ባቢሎን የተነገሩት እነዚህ ትንቢቶች ያለአንዳች ስሕተት እንዴት እንደተፈጸሙ ስናይ እንደነቃለን። ትንቢቱ እንዳመለከተው፥ ዛሬ ባቢሎን የሚባል ከተማ የለም፤ በረግረግ መካከል ያለ ፍርስራሽ ነው። እግዚአብሔር እስከወሰነ ትዕቢተኞች የሆኑ መንግሥታትንና መሪዎችን ለማዋረድ የሚያግደው ምንም ነገር የለም።

2. በአሦር ላይ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 14፡24-27)።

አሦር የመጀመሪያዋ የዓለም ታላቅ መንግሥት እንደነበረችና የሰሜኑን የእስራኤል መንግሥት የደመሰሰች መሆንዋን ታስታውሳለህ። እንዲሁም በኢሳይያስ ዘመን ከፍተኛ የዓለም መንግሥት በመሆን በይሁዳ ሕዝብ ላይ ታላቅ ጥፋትና መከራ አምጥታለች።

ይህ ትንቢት በተነገረ ጊዜ ታላቅ መንግሥት የነበረች ብትሆንም፥ በ150 ዓመታት ውስጥ እንደምትወድቅ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር የአሦርን መንግሥት መውደቅ ለማመልከት በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ ልዩ ትኩረት አልሰጠውም።

3. በፍልስጥኤም ላይ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 14፡28-32)

ከይሁዳ መንግሥት የረጅም ጊዜ ጠላቶች አንዱ የፍልስጥኤም መንግሥት ነበር። ፍልስጥኤም በአይሁድ የተያዘችው በዳዊት ዘመነ መንግሥት ነበር። ሆኖም ዕድል ባገኘች ቊጥር፥ ፍልስጥኤም በአይሁድ ላይ በማመፅ፥ ይሁዳን ለማጥቃት ከይሁዳ ጠላቶች ጋር ብዙ ጊዜ ትተባበር ነበር። በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ፍልስጥኤም በአሦር ስለ መወረርዋና ስለመደምሰሷ ተነበየ።

4. በሞዓብ ላይ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 15-16)

ከጥንት የአይሁድ ጠላቶች አንድዋ ሞዓብ ነበረች። ከዳዊት ዘመን በኋላ በነበረው አብዛኛው ታሪኳ ሞዓብ በእስራኤል ወይም በይሁዳ ቊጥጥር ሥር ነበረች። አጋጣሚ ጊዜ ባገኘበት ጊዜ ሁሉ ግን ታምፅ ነበር። የይሁዳ

ጠላቶች ኢየሩሳሌምን ለማጥቃት በተነሡበት ጊዜ ሁሉ ሞዓብ ትተባበር ነበርና እግዚአብሔር ሽንፈቷንና ጥፋቷን አስቀድሞ ተናገረ። ይህ ትንቢት ሞዓብ በባቢሎን መወጋቷንና መሸነፏን የሚያመለክት ቢሆንም እንኳ ዋናው አሳብ ግን በአሦር መንግሥት ስለሚደርስባት ጥፋት የተነገረ ሳይሆን አይቀርም።

5. በደማስቆ ወይም በሶርያ ላይ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 17)

ደማስቆ የአራም ወይም የሶርያ መንግሥት ዋና ከተማ እንደሆነች ታስታውሳለህ። ኢሳይያስ በኖረበት ዘመን፥ በተለይ ደግሞ በአካዝ ዘመነ መንግሥት የሶርያ መንግሥት ከእስራኤል ጋር በመተባበር ይሁዳን ለማጥቃት ውጊያ አካሂዶ ነበር። የሶርያ ሕዝብ የአይሁድ ሕዝብ ታሪካዊ ጠላት ነበሩ (ለምሳሌ፡- 1ኛ ነገሥት 20)። እግዚአብሔር ሶርያ በተለይም ደግሞ ዋና ከተማዋ ደማስቆ በቅርቡ እንደምትደመሰስ ተናግሮ ነበር። ይህም በ732 ዓ.ዓ. አሦራውያን ከተማዋን ባጠፏትና ብዙ ሕዝብ ማርከው በወሰዱበት ወቅት ተፈጸመ። በዚህ ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ ከሶርያ ጋር ተባብረው ነበር። ስለዚህ በዚህ ክፍል በተነገረው ትንቢት ውስጥ የሰሜኑ መንግሥት ተጨምሮ ነበርና እግዚአብሔር እስራኤልም ትደመሰሳለች በማለት ተናገረ።

6. በኩሽ ወይም በኢትዮጵያ ላይ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 18)

በጥንት ዘመን ኩሽ ተብሎ ይጠራ የነበረው ሕዝብ ከገናናው የግብፅ መንግሥት በስተደቡብ ይገኝ የነበረው ነው። ይህች አሁን አገራችን የምትጠራበት ያለችው በጥንታዊ ግሪክም «ኢትዮጵያ» በሚለው ስም ትጠራ ነበር። ይሁን እንጂ የጥንቱ የኩሽ ወይም የኢትዮጵያ ግዛት ከዛሬው የኢትዮጵያ ግዛት ጋር አንድ አይደለም።

የኩሽ ሕዝብ ከይሁዳ እጅግ ርቆ የሚገኝ ሕዝብ ነበር። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ፍርድ ሥር ወደቀ። ይህም ሊሆን የቻለው የኩሽ ምድር ሰዎች ከጠላቶቻቸው ጋር የሚዋጉት ብዙ ጊዜ ከግብፅ ጋር በመተባበር ስለነበረ ነው። እንዲያውም በ715 ዓ.ዓ. ከኩሽ የመጣ ሰው የግብፅ መሪ ሆኖ ነበር። የግብፅ ምድር መጀመሪያ በአሦር በኋላም በባቢሎን እንደተወረረች ሁሉ፥ የኩሽ ምድርም የእግዚአብሔርን ፍርድ የቀመሰችው በዚህ መንገድ ነበር፤ ነገር ግን አንድ ቀን የዚህ ምድር ሰዎች እግዚአብሔርን እንደሚያከብሩና ለእርሱ ስጦታን ይዘው ወደ ጽዮን

እንደሚመጡ ኢሳይያስ ተንብዮአል። ይህ ትንቢት መሢሑ ሊገዛ በሚመጣበት በዘላለማዊው ጊዜ መንግሥት እንደሚፈጸም አያጠራጥም።

7. በግብፅ ላይ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 19-20)

የጥንቷ ግብፅ በጥበቧ፥ በኃይሏና በሥልጣኔዋ የምትታወቅ ነበረች። እግዚአብሔር ሊፈርድባት በወሰነ ጊዜ ግን እነዚህ ሁሉ ከንቱ ሆኑ። እግዚአብሔር አሦራውያንን ቢጎላም ደግሞ ባቢሎናውያንን በመጠቀም በግብፅ ትዕቢት ላይ ፈረደና አዋረዳት።

እንደገና እግዚአብሔር ወደ መጨረሻው ዘመን የሚያመለክተውን፥ የግብፅን ደኅንነት በሚመለከት አስቀድሞ ተናገረ። ግብፆች ወደ እስራኤል በመምጣትና እግዚአብሔርን በማምለክ ያከብሩታል። ጥንት ጠላቶች በነበሩት በአሦርና በግብፅ መካከልም ሰላም ይሆናል፤ ሁለቱም ከእስራኤል ጋር በመሆን የእግዚአብሔር ሕዝብ ተብለው ይጠራሉ።

> 5ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ወደፊት አሕዛብ በሙሉ እግዚአብሔርን እንደሚያከብሩና እግዚአብሔርም ከእስራኤል እኩል የተመረጡ ሕዝቦች አድርጎ እንደሚቈጥራቸው እነዚህ ቊጥሮች ምን ያስተምሩናል? ለ) ይህ ነገር ለእኛ ትልቅ ማበረታቻ የሚሆነንና በተስፋ ወደፊት እንድንጠብቀው የሚያደርገን እንዴት ነው?

በኢሳይያስ 20 አሦርን ለመውጋት ከግብፅ ጋር እንዳትተባበር ወይም ተስፋዋን በግብፅና በኩሽ ጦር ላይ እንዳታደርግ እግዚአብሔር ይሁዳን ይመክራታል ምክንያቱም የእነርሱም ጦር ስለሚደመሰስ ነው። ኢሳይያስ ለሦስት ዓመታት እንደ ባሪያ በመልበስና በባዶ እግሩ በመመላለስ ይህንን በተግባር አሳየ።

8. በባቢሎን ላይ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 21፡1-10)

ባቢሎን በሜዶን እንደምትደመሰስ እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ ይናገራል።

9. በኤዶም ላይ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 21፡11-12)

ኤዶምም ከጥንት የእስራኤልና የይሁዳ ጠላቶች መካከል አንዱ ነበረች። እግዚአብሔር ምሳሌዎችን በመጠቀም፥ በኤዶም ምድር ላይ ጨለማ እንደሚሆን ተንብዮአል። ይህ ኤዶም በአሦርና በባቢሎን ስለ

መደምሰሷ የሚናገር ነው። ገና ማለዳ በሚመስልበት ወቅት የአሦር ጥፋት ይመጣል፤ የባቢሎን ምርኮ ጨለማም በእነርሱ ላይ ይሆናል።

10. በዐረብ ላይ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 21፡13-17)

የዐረብ ምድር በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሽንፈት እንደሚገጥመውና እንደሚመታ እግዚአብሔር አስቀድሞ ተናገረ። በ732 ዓ.ዓ. አሦራውያን፥ ዲዳናይቶች በመባል ይታወቁ የነበሩትን የዐረብ ነጋዴዎች መውጋት ጀመሩ፤ በኋላም ባቢሎናውያን ይህንኑ አደረጉ።

11. በኢየሩሳሌም ላይ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 22)

እግዚአብሔር በአሕዛብ ላይ ፍርድን በሚያመጣበት ጊዜ፥ በምርጥ ሕዝቦቹ በአይሁዳውያን ላይ ፍርድን አያመጣም ማለት አይደለም። ኢሳይያስ ወደ ይሁዳና ወደ ዋና ከተማዋ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ ጥፋቷ እንደቀረበ በመተንበይ ይህንን አስታወሳቸው። እግዚአብሔር እንደ ኢሳይያስ ላሉ ነቢያት ራእይን የሚሰጠው በኢየሩሳሌም ስለነበር ኢየሩሳሌም «የራእይ ሸለቆ» በመባል ተጠርታለች። እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደተናገረው ኢየሩሳሌም፥ አሦራውያን ከሚያመጡት ጥፋት ልታመልጥ ብትችልም፥ ባቢሎናውያን እነርሱን በምርኮ ለማጋዝ ከሚያመጡት ጥፋት ግን አታመልጥም።

12. በጢሮስ ላይ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 23)

የጢሮስና የሲዶና ትንንሽ የከተማ መንግሥታት በጥንት ዘመን የነበሩ ሁለት ትልልቅ ከተሞች ናቸው። የጢሮስና የሲዶና ሰዎች ፊንቄያውያን በመባል ይታወቁ ነበር። በመላው ሜዲተራኒያን ባሕር በመርከብ እየተዘዋወሩ በመነገድ ችሎታቸው የታወቁ ነበር። ጢሮስ ባለጠጋ አገር ሆነች። እንዲሁም ልትጠፋና ልትደመሰስ እንደማትችል ባሰበችው መንገድ የተገነባች ነበረች። የጢሮስ ከተማ አንዱ ክፍል በየብስ ላይ፥ ሌላው ክፍል ደግሞ በውኂያ አንሸነፍም ባሉበት በሜዲተራኒያን ባሕር ደሴት ላይ የተመሠረተች ነበረች። ይህም የጢሮስን ሰዎች በራሳቸው እጅግ እንዲታበዩ አደረጋቸው።

ብዙ ጊዜ ጢሮስና ይሁዳ በሰላም የቆዩ ነበሩ። እግዚአብሔር ግን ጢሮስን በከፍተኛ ትዕቢትና በክፉ የጣዖት አምልኮዋ ምክንያት ጠልቷት ነበር። የበዓል አምልኮ የተጀመረው በጢሮስ ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ጢሮስን ሊያጠፋት ወሰነ። በየብስ ላይ ተገንብቶ የነበረው ዋናው የከተማዋ

ክፍል በ572 ዓ.ዓ. በናቡከደነፆር ሲደመሰስ፥ በደሴት ላይ የነበረው የከተማዋ ክፍል ደግሞ በ332 ዓ.ዓ. በታላቁ እስክንድር ተደመሰሰ። ስለ ጢሮስ ጥፋት ሕዝቅኤል ከዚህ ይልቅ ዘርዘር ባለ ሁኔታ ይተነብያል (ሕዝቅኤል 26-28)።

ታላቅ የሆነው የእግዚአብሔር እጅ ማንም ሊያጠፋን አይችልም በማለት ይመካ የነበረውን ይህን ትዕቢተኛ ሕዝብና መሪዎቹን በማዋረድ ታሪክን እንደሚቈጣጠር እንደገና እንዳሳየ እናያለን።

6ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ስለ እግዚአብሔር እንዲሁም ሕዝቦችንና መሪዎችን ስለ መቈጣጠሩ ከእነዚህ ምዕራፎች ምን እንማራለን? ለ) በመንግሥታትና በመሪዎች ቍጥጥር ሥር የሚኖሩትን ክርስቲያኖች ይህ እውነት የሚያበረታታቸው እንዴት ነው? ሐ) እግዚአብሔር ትዕቢትን የሚጠላው ለምን ይመስልሃል? መ) ዛሬ ሕዝቦች ወይም መንግሥታት ሊታበዩ የሚችሉባቸው መንገዶችን ጥቀስ። ሠ) ብዙ ክርስቲያኖች ሊታበዩ የሚችሉት እንዴት ነው? የሚታበዩትስ ለምንድን ነው?

2ኛ ቀን፡- ኢሳይያስ 24-39

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚቀርቡ ስብከቶችና ትምህርቶች ውስጥ የሚተላለፉ መልእክቶችን ውጤታማ ከሚያደርጓቸው ቍልፍ ጉዳዮች አንዱ መልእክቶቹ የጠፉትን የማዳንና ክርስቲያኖችን የማስተማር ሚዛናዊነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ነው። ስብከቶቻችን በሚያበረታታና ተስፋ በሚሞላ፥ እንዲሁም ስለ ፍርድ በሚናገር መልእክት መካከል ሚዛናዊ መሆን አለባቸው።

7ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16ን በቃልህ አጥና። ሀ) የእግዚአብሔር ቃል ለምን እንደሚጠቅም ዘርዝር። ለ) ለክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል የመጨረሻ ውጤት ምንድን ነው? ሐ) ባለፉት ሦስት ወራት በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የተሰበኩ ስብከቶችን ወይም አንተ ራስህ ባለፈው አንድ ዓመት የሰበከውን ስብከት አስታውስ። የእግዚአብሔር ቃል የሚጠቀምባቸውን የተለያዩ የሕይወት ክፍሎች (አቅጣጫዎች) በመጠቀም፥ የትኛው መልእክት ለየትኛው ዓይነት ጥቅም እንደታለመ ግለጽ።

(ለምሳሌ፡- የደኅንነት መልእክትና ትምህርት)። መ) ብዙ ጊዜ ባለመሰበኩ ምክንያት ትምህርቱን ሚዛናዊ ያላደረገው የትኛው ዓይነት መልእክት ነው? ሠ) የሚሰጠው ትምህርት የበለጠ ሚዛናዊ ይሆን ዘንድ አንተ ወይም ቤተ ክርስቲያንህ ማቅረብ የሚገባችሁ አንዳንድ ርእሰ-ጉዳዮችን ጥቀስ።

ኢሳይያስ፥ እንደ ብዙዎቹ ነቢያት መልእክቱን ሚዛናዊ አደረገው። ነቢዩ አንዳንድ ጊዜ ሕዝቡን ለክፉና ኃጢአተኛ ለሆነው ሕይወታቸው በብርቱ ሲገሥጻቸው፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ የሚያጽናና የሚያበረታታ መልእክት ይነግራቸው ነበር። አንዳንድ ጊዜ ነቢያት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በቅርቡ ስለሚፈጸም ፍርድ ያመለክቱ ነበር። በሌላ ጊዜ ደግሞ ነቢያት በዓለም ላይ የሚገኝ ክፉት ሁሉ ስለሚደመሰስበትና እግዚአብሔር ስለሚነግሥበት የመጨረሻ ዘመን ይናገሩ ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰብኩና የሚያስተምሩ ሰዎች በብሉይ ኪዳን የነበሩትን ነቢያት ምሳሌነትን ለመከተል በጣም ጠንቃቃዎች መሆን አለባቸው። ስለ መንፈሳዊ ስንፍናውና ስለ ቅድስና ጕድለት የእግዚአብሔርን ሕዝብ መገሠጽ የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። እንዲሁም ሕዝቡ እግዚአብሔርን በመከተሉ ሊመሰገንና ከዚያ በላቀ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ጋር በቅርብ ተሳስሮ እንዲራመድ ሊበረታታ የሚገባውም ጊዜ መኖር አለበት።

ኢሳይያስ ከምዕራፍ 24 እስከ 39 ባለው የመጽሐፉ ክፍል የፍርድና የማጽናኛ ወይም የማበረታቻ መልእክቱን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ አቅርቦታል።

8ኛ ጥያቄ፥ ኢሳይያስ 24-39 አንብብ። ሀ) በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የፍርድ መልእክቶችን ዘርዝር። ፍርዶቹ ምንድን ናቸው? ለ) በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ የማበረታቻ መልእክቶች ዘርዝር። የተሰጡት የተስፋ ቃሎች ምንድን ናቸው? ሐ) ከኢሳይያስ 36-39 የተገለጹ ታሪካዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው? እነዚህ ምዕራፎች በኢሳይያስ ትንቢት ላይ ተጨማሪ ነገሮችን የሚያክሉት እንዴት ነው?

የትንቢተ ኢሳይያስ አራተኛው ዐቢይ ክፍል ከምዕራፍ 24-35 ነው። እነዚህ ምዕራፎች እጅግ የተለያዩ መልእክቶችንና የወደፊቱን ሁኔታ የሚያመለክቱ ትንበያዎችን ይዘዋል።

1. ኢሳይያስ 24፥ እግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥቱን ከመጀመሩ በፊት፥ በምድር ላይ ያለው ዘመን ስለሚያከትምበትና በሩቅ ስላለ የፍርድ ጊዜ የሚናገር መልእክት ነው። እግዚአብሔርን በመቃወም የሚቆሙ ሁሉ፥ ማለት መንግሥታት፥ ነገሥታት፥ አጋንንትም ሳይቀሩ (በከፍታ ያሉ ኃይላት ኢሳይያስ 24፡21) እንደሚደመሰሱ ይናገራል።

9ኛ ጥያቄ፥ ክፉ የሆኑ ሁሉ እንደሚደመሰሱ የተሰጠው ማረጋገጫ፥ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ሕይወት ይኖሩ ዘንድ ማበረታቻ የሚሆነው እንዴት ነው?

2. ኢሳይያስ 25-27 የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያጽናኑ መልእክቶች ናቸው። እግዚአብሔር የማጽናናት አምላክ ነው፤ ለድሆች መሸሸጊያ የሚሆን ታማኝም ነው። በችግር ጊዜ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይረዳል። በችግርና በጥፋት ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ ሰላም የማግኘት ምሥጢሩ አእምሮአችንን በእግዚአብሔር ላይ ማድረግ ነው። እርሱ ውስጣዊ ሰላምና ዋስትናን ይሰጠናል (ኢሳይያስ 26፡3-4 ተመልከት)። አንድ ቀን ሞት ይደመሰሳል። የክፋት መጋረጃ ከምድር ላይ ይወገዳል።

3. ኢሳይያስ 28-31 የፍርድንና የተስፋን መልእክቶች አዋሕዶ ያቀርባል። ሦስት ዐበይት ፍርዶች ታውጀዋል፤ በመጀመሪያ፥ በኤፍሬም ላይ የተደነገገ ፍርድን እናያለን። ኤፍሬም የእስራኤል ሰሜናዊው መንግሥት ሌላ ስም ነው። (ኢሳይያስ 28) ኢሳይያስ እስራኤል ፈጥና እንደምትጠፋ ተነበየ። ኢሳይያስ ሕዝቡን ወደ ክፋት በመሩት በእስራኤል መሪዎች ላይ እንዴት ትኩረት እንዳደረገ አስተውል። ካህናትንና ነቢያትን ስለ ስካር ያወግዛል፤ ነገር ግን የጽዮን የመሠረት ድንጋይ ወደሆነውና ሊመጣ ወዳለው መሢሕ ዳግም ያመለክታል።

ሁለተኛ፥ በዳዊት ከተማ ላይ ፍርድ ይመጣል። የዳዊት ከተማ የደቡቡ መንግሥት ዋና ከተማ የሆነችው የኢየሩሳሌም ሌላ ስም ነው (ኢሳይያስ 29-30)። ኢየሩሳሌም ትዋረዳለች እንጂ አትጠፋም፤ ዳሩ ግን

ኢየሩሳሌም ልትጠፋ በተቃረበችበት ጊዜ ጠላቶችዋ ይደመሰሳሉ። ይህ የሚያመለክተው የአሦርን ጦር መደምሰስ እንደሆነ አያጠራጥርም (ኢሳይያስ 37)። ኢየሩሳሌም ፍርድ ልትቀበል የነበረችበት ምክንያት ሕዝቡ በከንፈራቸው እግዚአብሔርን እናከብራለን ቢሉ እንኳ እግዚአብሔርን የሚያመልኩት በባዶ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ብቻ ስለነበር ነው። እግዚአብሔርን ከልባቸው አያመልኩትም ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝቦች እግዚአብሔርን በእውነት የሚያመልኩበት ጊዜ ግን ይመጣል።

10ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬም እኛ እግዚአብሔርን ከልባችን ሳይሆን በከንፈራችን ብቻ ማምለክ ቀላል የሚሆንልን እንዴት ነው? ምሳሌዎችን ጥቀስ። ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ መሆንህ መጠን ሕዝቡ በከንፈሩ ብቻ ሳይሆን በልቡም ጭምር እግዚአብሔርን እንዲያመልክ ምን ማድረግ ትችላለህ?

ሦስተኛ፥ ከጠላቶቻቸው ከአሦራውያን ያድኗቸው ዘንድ በእግዚአብሔር ላይ ከመታመን ይልቅ፥ በግብፅ ላይ በሚታመኑ ሰዎች ላይ ፍርድ ይመጣባቸዋል። አይሁድ የአሦር ጦር ኢየሩሳሌምን ለመውጋት በመጣ ጊዜ በጦርነቱ ይረዳቸው ዘንድ እጅግ ታላቅ ጦርና በርካታ ፈረሶች ያሉትን የግብፅን መንግሥት ለመጠየቅ በጣም ተፈትነው ነበር። እግዚአብሔር ግን ይህንን እንዳያደርጉ በኦሪት ዘዳግም አስጠንቅቆአቸው ነበር። ይልቁንም ነፃ እንዲያወጣቸው በእግዚአብሔር ላይ መታመን ነበረባቸው።

11ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬም እኛ በእግዚአብሔር ላይ ከመታመን ይልቅ በሌሎች ሰዎች፥ በመንግሥታት ወይም በውጭ ዜጎች እንዴት ልንታመን እንችላለን? ለ) ይህስ በእግዚአብሔር ላይ ስላለን እምነት ምን ይናገራል?

4. የሚመጣው የጽድቅ ንጉሥ (ኢሳይያስ 32)፡- የዓለም ተስፋ ሰብአዊ መንግሥት ወይም ሰብአዊ ንጉሥ አይደለም። እነዚህ ልክ እንደ እኛ ኃጢአተኞችና ደካሞች ስለሆኑ ሁልጊዜ ተስፋ ያስቈርጡናል። ከዚህ ይልቅ ተስፋችን ሊመጣ ባለው የጽድቅ ንጉሥ-በጌታ ኢየሱስ

ክርስቶስ ላይ መሆን አለበት። በእርሱ የጽድቅ ዘመን መንግሥት እውነተኛ ሰላም ይኖራል።

5. ፍርድና በረከት (ኢሳይያስ 33-35)፡- ቀሪው የዚህ ክፍል ምንባብ ሊመጣ ያለውን ፍርድ፥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ከተዘጋጁ የወደፊት አስደሳች የተስፋ ቃሎች ጋር አጣምረው የያዙትን ትንቢቶች ያካትታል። ፍርዱ በፍጥነት እንደሚሆን ይናገራል። ይህ የሚያመለክተው የአሦርንና የባቢሎንን ምርኮ ነው፤ ነገር ግን ነፃ የወጡት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር በሰላምና በደኅንነት የሚኖሩበትንና ክፉት የሚደመሰስበትን የመጨረሻውን ጊዜ ደግሞ ያመለክታል።

የትንቢተ ኢሳያይስ የመጀመሪያ ዐቢይ ክፍል የሆነው ከምዕራፍ 1-39 ያለው አሳብ የሚጠቃለለው ታሪካዊ በሆነ አቀራረብ ነው። በዚህ ታሪክ ውስጥ ሁለት ዐበይት ታሪካዊ ድርጊቶች ይገኛሉ። በመጀመሪያ፥ አሦር ኢየሩሳሌምን የወጋችበት ታሪካዊ ድርጊት አለ። ይህ ለሕዝቡ ሁሉ የኢሳይያስን መልእክት ትክክለኛነትና እውነተኛነት የሚያመለክት ስለሆነ በጣም ጠቃሚ ነበር። ኢሳይያስ እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ላይ እንደሚፈርድና ዳሩ ግን ጨርሰው እንደማይጠፉ ተናገረ። አሦራውያን ይሁዳን ሊወጉ በወጡ ጊዜ ከኢየሩሳሌም በስተቀር ሁሉም ከተሞች ፈራረሱ። በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ሰዎች ወደ አሦር ተጓዙ። እግዚአብሔር ግን ከተማይቱ እንደማትወድቅ የገባውን ቃል አከበረ። ያለምንም የውጭ ጦር እርዳታ ጌታ ራሱ የአሦራውያንን ጦር ደመሰሰ። እርሱ ጠባቂያቸው እንደሆነና በእርሱ ብቻ ሊደገፉ እንደሚገባ እግዚአብሔር ለሕዝቡ አረጋገጠ።

ሁለተኛው ታሪካዊ ክሥተት የሕዝቅያስ ሕመም ሲሆን፥ እርሱም ከትንቢተ ኢሳይያስ ሁለተኛ ግማሽ ክፍል ጋር ያስተዋውቀናል። ሊመጣ ያለው የባቢሎን ምርኮ እርግጠኛ ነገር መሆኑን ያሳየናል። ሕዝቅያስ በታመመ ጊዜ እራስ ወዳድነቱ ዕድሜ እንዲጨመርለት እንዲጸልይ አደረገው። ሕዝቅያስ እስከዚህ ዘመኑ ድረስ እግዚአብሔርን የሚፈራ የመልካም ንጉሥ ሕይወት ምሳሌነት የሞላበት ኑሮ ስለኖረ በዚህ ሕመሙ ወቅት ቢሞት ይሻል ነበር። በስተ እርጅናው የታየው ራስ ወዳድነት ግን የሞኝነት ተግባር እንዲፈጽም አድርጎት ራሱንና ሕዝቡን አዋረደ።

የነበረውን ሀብት በሙሉ ለባቢሎናውያን በማሳየት፥ በሕዝቡ ላይ የወደፊት ጥፋት ጋበዘ። ያደረገው ነገር ቢኖር ስለ ራሱ በስስታምነት ማሰብ፥ እንደማይሞትና በዘመኑ ክፉ እንደማይመጣ በመመኘት መጽናናት ብቻ ነበር። አብዛኛውን የሕይወት ዘመናችንን እግዚአብሔርን ከተከተልን በኋላ እግዚአብሔርን፥ ራሳችንና ሕዝባችንን የማያስከብር ጥበብ የጐደለው ተግባር መፈጸም እጅግ ቀላል ነው።

ክፉው ንጉሥ ምናሴ የተወለደውም በዚህ ጊዜ ነበር። ከይሁዳ ነገሥታት ሁሉ የከፋ ሰው ነበር። ሕዝቅያስ በዚያን ጊዜ ሞቶ ቢሆን ኖሮ ይሁዳ ከዚህ ሁሉ ጥፋት ለማምለጥ በቻለች ነበር።

12ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር በታማኝነት ሲጓዙ ቆይተው ድንገት የወደቁና እግዚአብሔርን፥ ቤተሰባቸውንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያሰደቡትን ሰዎች እንዴት አይተሃቸዋል? ለ) ይህ ነገር ለእኛ ማስጠንቀቂያ ሊሆን የሚገባው እንዴት ነው?

3ኛ ቀን፡- ኢሳይያስ 40-49

የትንቢተ ኢሳይያስ ሁለተኛ ግማሽ ክፍል ለብዙ ክርስቲያኖች እጅግ ተወዳጅ ከሆኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል መካከል የሚመደብ ነው። ስለ ፍርድ የሚናገሩት ባለፉት መልእክቶች አብቅተዋል። ኢየሩሳሌምን የሚያጠፋው የባቢሎን ፍርድ በእርግጥ የሚፈጸም መሆኑን ኢሳይያስ አውቋል፤ ስለዚህ ምርኮው እንደተፈጸመ አድርጎ በመቍጠር ይጽፋል። ራሳቸው በምርኮ ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን በሚያጽናና መንገድ ይጽፋል።

ኢሳይያስ ሕዝቡን በሦስት መንገዶች ለማበረታታት ይፈልጋል፡-

በመጀመሪያ፥ የእግዚአብሔርን ታላቅነትና እግዚአብሔር በአሕዛብ፥ በምድር ነገሥታት፥ በአሕዛብ አማልክትና በሕዝቦቹ ሕይወት ውስጥ በሚፈጸሙ ድርጊቶች ሁሉ ላይ ያለውን ሉዓላዊ ሥልጣን ያለማቋረጥ በማመልከት ያበረታታቸዋል።

ሁለተኛ፥ ኢሳይያስ በምርኮ አገር ያሉ አይሁድ ወደገዛ ምድራቸው እንደሚመለሱ በማመልከት ያበረታታቸዋል። እግዚአብሔር ያኔም ቢሆን

ለይሁዳ ሕዝብ ዓላማ ነበረው፤ ስለዚህ የአይሁድ ሕዝብ በሙሉ እንዲጠፉ አይፈቅድም። ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ቅሬታዎች ይኖራሉ። እግዚአብሔርም ከእነዚህ ቅሬታዎች ጋር ይሠራል፤ ይጠብቃቸዋል፤ እንዲሁም ወደ ምድራቸው ይመራቸዋል።

ሦስተኛ፥ ሊመጣ ወዳለው «የእግዚአብሔር አገልጋይ» በማመልከት ያበረታታቸዋል። በዚህ የትንቢተ ኢሳይያስ የመጨረሻ ክፍል፥ ሊመጣ ወዳለው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያመለክቱ በርካታ ትንቢቶች ይገኛሉ። የእግዚአብሔር ሌላዋ አገልጋይ ከሆነችው ከእስራኤል በተቃራኒ፥ ይህ እውነተኛ አገልጋይ በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል ይመጣል፤ ጽድቅን ያደርጋል፤ ሕዝቡን ነፃ ያወጣል ስለ ኃጢአታቸውም ይሞታል።

13ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ሦስት እውነቶች በዚህ ዘመን ላለን ክርስቲያኖች ማበረታቻ የሚሆኑት እንዴት ነው? ለ) ከእነዚህ ሦስት ርእሶች፥ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች ለማበረታታት መልእክት ልታቀርብ የምትችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር።
14ኛ ጥያቄ፥ ኢሳይያስ 40-49 አንብብ። ሀ) በእነዚህ ቍጥሮች ውስጥ የእግዚአብሔር ታላቅነት የታየባቸውን የተለያዩ መንገዶች ዘርዝር። ለ) በእነዚህ ቍጥሮች ውስጥ እግዚአብሔር በምርኮ ላይ ላሉት ሕዝቡ የሰጣቸውን የተለያዩ የማበረታቻ ተስፋዎች ዘርዝር። ሐ) በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ስለሚመጣው «የእግዚአብሔር አገልጋይ» የተጠቀሱትን የተለያዩ እውነቶች ዘርዝር።

በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ያለማቋረጥ የምናያቸው ሁለት ዐበይት አሳቦች አሉ። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔርን ለማወቅ በሚመለከት ዋና አሳብ እናገኛለን። ዳንኤል 11፡32 እንዲህ ይላል፡- «...ነገር ግን አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ይበረታሉ፥ ያደርጋሉም» (ሐሰተኛ ክርስቶስን ይቃወማሉ)። እኛ ክርስቲያኖች በታላቅ መከራና ችግር በተሞላችው በዚህች ዓለም ውስጥ በሙሉ ልብነትና በደስታ ልንመላለስ የምንችለው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፥ ምን እንደሚመስል፥ ምን እንደሚፈልግና የሰጠን ቃል ኪዳን ምን እንደሆነ በምናውቅበት ጊዜ ነው። ችግሩ ግን እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፥ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነና ምን

ያህል እንደሚወደን ግልጽ የሆነ መረዳት ያላቸው ጥቂት ክርስቲያኖች ብቻ መሆናቸው ነው። እነዚህ እውነቶች ይበልጥ ግልጽ በሆኑልን ቍጥር፥ የምንቀበለው መጽናናትና መበረታታትም እየጨመረ ይሄዳል። ኢሳይያስ በምርኮ የነበሩት እስራኤላውያን ዓይኖቻቸውን ወደ እግዚአብሔር እንዲመልሱ ያበረታታቸዋል። እግዚአብሔር በፍጥረታት፥ በአሕዛብ፥ በነገሥታት፥ በአሕዛብ የውሸት አማልክት ላይ እንኳ ታላቅ እንደሆነ ይነግራቸዋል። እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን ፍቅርና የወደፊት ዓላማ ይነግራቸዋል። ተስፋ በምንቈርጥበት በማንኛውም ጊዜ ወደ ትንቢተ ኢሳይያስ ሁለተኛ ክፍል ብንመለስና ትኩረታችንን በእግዚአብሔር ላይ ብናደርግ እንጽናናለን፤ ብርታትንም እናገኛለን።

ሁለተኛው ዋና አሳብ፥ «የእግዚአብሔር አገልጋይ» የሚለው ነው። በክፍሉ የተጠቀሱ ሁለት የተለያዩ አገልጋዮች አሉ፡-

1. የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነው የእስራኤል ሕዝብ (ኢሳይያስ 41፡8-10)፡- የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነችው እስራኤል ብዙ ጊዜ ብትወድቅም፥ እግዚአብሔር ግን አልተዋትም። ይልቁንም እግዚአብሔር በምድር ላይ ከሚገኙ አሕዛብ ሁሉ መርጦ እስራኤልን ጠራት፤ ከእርሷ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፤ ምንጊዜም እንደማይተዋት ተስፋ ሰጣት። እግዚአብሔር እስራኤልን ይጠብቃታል፤ ይመራታል፤ የሚያስፈልጋትን ሁሉ ያደርግላታል። ወደ ቀድሞ ክብሯም ይመልሳታል። ቂሮስ የተባለ ሌላ አገልጋዩን በማስነሣት፥ ሕዝቡን ወደ ነፃነቱ ይመራዋል። እንደ ቤልና ኔቦ ያሉትን የባቢሎናውያን አማልክትና ባቢሎናውያንን ይደመስሳል።

2. የእግዚአብሔር አገልጋይ የተባለው ሊመጣ ያለው የእስራኤል መሪ፡- ይህ አሳብ በቀሪው ኢሳይያስ ክፍል ውስጥ በሙሉ በመቀጠል የሚገኝ ነው (ኢሳይያስ 42፡1-7፤ 49፡1-7፤ 50፡4-9፤ 52፡13-53፡12)። ይህ እንደ ልቡ የሆነው የእግዚአብሔር አገልጋይ በመንፈስ ቅዱስ የሚሞላና በድድቅ የሚነግሥ ነው። የዕውሮችን ዓይን በማብራትና ምርኮኞችን ነፃ በማውጣት፥ ለአሕዛብ ብርሃን ይሆናል። ከእግዚአብሔር የተማረና ሌሎችንም የሚያስተምር ይሆናል። በዚህም ዓይነት ለደከሙት ብርታትን ይሰጣቸዋል። ቤሌላ

በኩል ደግሞ ሰዎች ያሳድዱታል ይገድሉታልም። በዚህ መልኩ ደግሞ ለብዙዎች ደኅንነትን ያመጣል።

15ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ለእግዚአብሔር እንደ ልቡ ስለሆነው አገልጋይ የተነገሩትን እነዚህን እውነቶች ኢየሱስ ክርስቶስ የሚፈጽመው እንዴት ነው? ለ) እኛስ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር እንደ ልቡ አገልጋይ እንደሆነው እንዴት እንሆናለን? ሐ) እኛም የእግዚአብሔር አገልጋዮች መሆን አለብን (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡24 ተመልከት)። ይህ ማለት ምን ማለት ነው? ይህ የዕለት እርምጃችንን የሚለውጠው እንዴት ነው?

4ኛ ቀን፡- ኢሳይያስ 50-66

16ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ክርስቲያኖች በመከራ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ ስለ ዘላለማዊ መንግሥት መማር የሚያስፈልጋቸው ለምን ይመስልሃል? ለ) እግዚአብሔር ስለ መጨረሻው ዘመን ያለውን ዕቅድ የቤተ ክርስቲያንህ አባሎች ምን ያህል ተረድተውታል ብለህ ታስባለህ? ሐ) ስለ መጨረሻው ዘመን በተሻለ ሁኔታ ለማስተማር ምን ማድረግ ትችላለህ?

ክርስቲያኖች አስቸጋሪና አስጨናቂ በሆነ ሁኔታ ውስጥ በሚገኙበት ጊዜ እግዚአብሔር ስለ መጨረሻው ዘመን ያለውን ዕቅድ መረዳት ይጠቅማቸዋል። የምንወዳቸው በሞት ሲለዩን፥ በስደት ጊዜ ወይም ድርቅና ራብ ሲኖር እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን ምን ዕቅድ እንዳለው መረዳት አስፈላጊ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አንድ ቀን በጽድቅና በእውነተኛ ፍርድ በእኛ ላይ እንደሚነግሥ ማስታወስ አስፈላጊ ነው። በዚያ ድህነት፥ ሞት፥ ጦርነትና በሽታ አይኖርም። ክፉዎች ሁሉ ይደመሰሳሉ፤ የነገድና የጎሳ ጦርነትም ይቆማል። በመጀመሪያው ሰው በኃጢአት መውደቅ ምክንያት የተደመሰሰው ፍጥረት በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር ይተካል። ዓይኖቻችንና አስተሳሰባችንን በእነዚህ ነገሮች ላይ ካደረግን፥ አስቸጋሪ በሆኑት በእነዚህ ጊዜያት እንኳ በታላቅ ደስታ ልንኖር እንችላለን። ጳውሎስ እንዳለው፡- «ስለዚህ አንታክትም፥ ነገር ግን የውጪው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል። የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፥ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ

ያደርግልናልና የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው» (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡16-18)።

ትንቢተ ኢሳይያስ ስለ መጨረሻው ዘመንና እግዚአብሔር ሊመሠርተው ስላቀደው ዘላለማዊ መንግሥት ብዙ የሚናገረው ነገር አለው። በእዚያ ስለሚኖረው ሰላምና ደስታ የሚናገሩ ብዙ ምሳሌዎችን ይጠቀማል። ከእነዚህ ምሳሌዎች አብዛኛዎቹ በዮሐንስ ራእይ ውስጥ ይገኛሉ። ክርስቲያኖች ስለ መጨረሻዎቹ ዘመናት የሚናገሩትን እነዚህን ምንባቦች በተለያየ መንገድ ቢተረጕሟቸውም እንኳ እግዚአብሔር አንድ ቀን በፍጹም በላይነት እንደሚነግሥና ኃዘንና ጦርነት፥ ኃጢአትም ፍጹም እንደሚደመሰሱ ይስማማሉ።

17ኛ ጥያቄ፥ ኢሳይያስ 50-66 አንብብ። ሀ) ስለ መጨረሻዎቹ ጊዜያት የሚናገሩ ናቸው ብለህ የምታስባቸውን በዚህ ክፍል የሚገኙ የተለያዩ ትንቢቶችን ጥቀስ። ለ) ስለዚያ ዘመን ለእስራኤል ሕዝብ በዚህ ክፍል የተሰጠው ቃል ኪዳን ምንድን ነው? ሐ) ክርስቲያን እንደመሆንህ መጠን በአስቸጋሪና በአስጨናቂ ጊዜ እነዚህ ትንቢቶች መጽናናት የሚሰጡህ እንዴት ነው? መ) «ስለ እግዚአብሔር አገልጋይ» በዚህ ክፍል የተነገሩ ትንቢቶች የትኞቹ ናቸው?

በዚህኛው የኢሳይያስ መጽሐፍ ክፍል ውስጥ አራት ዋና ዋና ርእሶች ይገኛሉ፡-

1. ይህ ክፍል በዘመኑ መጨረሻ ስለሚሆኑ ነገሮች እግዚአብሔር በሰጣቸው ታላላቅ ተስፋዎች የተሞላ ነው። ስለ እስራኤል ሕዝብ መዳንና ስለ አይሁድ እግዚአብሔርን ማምለክ የተሰጡ ተስፋዎች አሉ፤ ስለ አሕዛብ መዳን የተሰጡ ተስፋዎችም አሉ። ስለ አዲስ ሰማይና ምድር የተሰጡ ተስፋዎች አሉ፤ ክፉዎች እንደሚፈረድባቸው የተነገረ የፍርድ ተስፋም አለ።

2. የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት፥ በጽድቅ የሚኖረው ሊመጣ ያለው «የእግዚአብሔር አገልጋይ» ስለ ዓለም ኃጢአት ብሎ ማንም ያልተቀበለውን መከራ ይቀበላል (50፡4-9፤ 52፡13-53፡12)።

3. ለተጠሙና ኃጢአታቸው ይቅር እንዲባልላቸውና ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ግንኙነት ማድረግ ለሚፈልጉ ሁሉ የተደረገ የደኅንነት ጥሪ እናገኛለን (ኢሳይያስ 55)።

4. ለእግዚአብሔር የሚቀርብ እውነተኛ አምልኮ ባሕርይና ከእግዚአብሔር እውነተኛ በረከትን የመቀበያ መንገድ (ኢሳይያስ 58)፡- እግዚአብሔርን ማምለክ በቅድሚያ በከንፈሮቻችን በመዘመርና በመጸለይ የምንፈጽመው ተግባር አይደለም፤ ወይም ደግሞ በየዕለተ እሑድ በቤተ ክርስቲያን በመገኘት የምንፈጽመው ሥርዓት አይደለም።

ይልቁንም እውነተኛ አምልኮ በእግዚአብሔር ፊት ከሚደረጉ ትክክለኛ ተግባራት የሚፈልቅ ነገር ነው። እውነተኛ አምልኮ ለጎረቤቶቻችን ቅንና አድልዎ የሌለበትን ተግባር ስንፈጽምና በአካባቢያችን ለሚገኙ ድሆች ርኅራኄንና ልግሥናን ስናሳይ ነው። ሌሎችን ለማገልገል ራሳችንን ስንሰጥ እግዚአብሔር ደግሞ በተራው በመንፈሳዊ ብርሃን ይባርከናል፤ ይመራናል፤ የሚያስፈልጉንም ነገሮች ሁሉ ይሰጠናል።

18ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔርን እያመለክህ የምትኖርባቸውን መንገዶች ግለጽ። ለ) ለጎረቤቶችህ ቅን ፍርድን እንዴት እንደምታሳይ የሚያስረዱ መግለጫዎችን ስጥ። ሐ) ባለህበት ጎብረተሰብ ውስጥ የሚገኙትን ድሆች ለመርዳት የጣርህባቸውን መንገዶች ግለጽ። መ) የዚህ ዓይነቱ ሕይወት በረከትን ያመጣልህና ለእግዚአብሔር ያለህን አምልኮ በጥልቀት ያሳደገው እንዴት ነው? ሠ) እግዚአብሔርን በእውነተኛ አምልኮ ታከብረው ዘንድ በዚህ ረገድ መሻሻል የምትችልባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው?

19ኛ ጥያቄ፥ እግዚአብሔር ከእነርሱ ምን እንደሚፈልግ የቤተ ክርስቲያንህን ሰዎች ለማስተማር በትንቢተ ኢሳይያስ እውነቶች እንዴት ልትጠቀም ትችላለህ?

5ኛ ቀን፡-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ዝግጅት ይረዱህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

ሳምንታዊ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ

2. ጸሎት

3. የትምህርቱ ክለሳ

4. የውይይት ጥያቄዎች

ሀ: 1) እግዚአብሔር በምድር አሕዛብ ላይ ስለሚያመጣው የወደፊት ፍርድ ኢሳይያስ ምን ያስተምረናል?

2) እግዚአብሔር በሰዎች ላይ የሚፈርደው ከምን አኳያ ነው?

3) አሕዛብ ወይም ገዥዎቻቸው በእኛ ላይ በሚነሡበት ጊዜ ይህ እንዴት ማበረታቻ ይሆነናል።

ለ. 1) ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር የሚያስተምረን የተለያዩ እውነቶች ምንድን ናቸው?

2) እግዚአብሔር ማን እንደሆነና ከእኛ ምን እንደሚፈልግ ክርስቲያኖች ግልጽ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖረን የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

3) ቤተ ክርስቲያንህ ምእመናኗን ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ በግልጽ ለማስተማር ምን ታደርጋለች?

4) ከኢሳይያስ ያገኘሃቸውንና ስለ እግዚአብሔር ባሕርይና ፈቃድ ስብከት ልታዘጋጅባቸው የምትችልባቸውን ርእሶችን ጥቀስ።

ሐ. ስለ አገልጋዩ የሚናገሩትን ክፍሎች በሙሉ እንደገና ከልስ። 1) የእግዚአብሔር አገልጋይ ስለሆነው ስለ ኢየሱስ ኢሳይያስ ምን ያስተምረናል?

2) ኢየሱስ የእግዚአብሔር አገልጋይ የተባለው ለምንድን ነው?

3) እነዚህ ክፍሎች እኛም የእግዚአብሔር አገልጋዮች ስለመሆናችን ምን ያስተምሩናል?

መ. ከትንቢተ ኢሳይያስ ንባብህ፥ በዘመኑ መጨረሻ የሚፈጸሙትን ነገሮች አንድ በአንድ ዘርዝር።

1) ከፉዎቹ ነገሮች ምንድን ናቸው? 2) መልካም የሆኑት ነገሮች ምንድን ናቸው?

3) እነዚህን ነገሮች ማወቅ ዛሬ ለእኛ ጥቅም የሚሰጠው እንዴት ነው?

5. ጸሎት

ትምህርት አሥር

1ኛ ቀን፡- የትንቢተ ኤርምያስ መግቢያ

1ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ታላቅ ክርስቲያን፥ የተዋጣለት ወንጌላዊ ወይም ሰባኪ፥ በአገልግሎቱና በግል ሕይወቱ ሁልጊዜ የሚከናወንለት ይመስልሃልን? መልስህን አብራራ። ለ) ክርስቲያኖች ከሆኑ ሕይወት እጅግ ቀላል እንደሚሆንላቸው፥ እግዚአብሔር ከበሽታ እንደሚጠብቃቸው፥ ሥራ እንደሚያገኙና ሀብታሞች እንደሚሆኑ አድርገው የሚያስቡ የምታውቃቸው ሰዎች አሉን? ይህ ነገር ሁልጊዜ እውን የሚሆን ይመስልሃል? ሐ) በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ ክርስቲያን ተስፋ አይቆርጥም ወይም እግዚአብሔርን አይጠራጠርም ብለህ ታስባለህን? መልስህን አብራራ።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ እጅግ በጣም ረጅሙ መጽሐፍ ትንቢተ ኤርምያስ ነው፤ ስለዚህ ክርስቲያኖች ከመጽሐፍ ቅዱስ ዐበይት መጻሕፍት መካከል እንደ አንዱ አድርገው እንደሚቈጥሩት እናምናለን። የሚያሳዝነው ግን ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በመጽሐፉ ውስጥ ምን እንደሚያስተምር ለማየት ትንቢተ ኤርምያስን ሲያነቡ ወይም ሲያጠኑ አይታዩም። ትንቢተ ኤርምያስ ለብዙዎቻችን የተደበቀ መጽሐፍ ነው። ስለሆነም እግዚአብሔር እንድናውቃቸው የሚፈልጋቸው በርካታ ጠቃሚ እውነቶች መጽሐፉን ባለማጥናታችን ተሰውረውብን ይኖራሉ።

በትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ የነቢዩ ኤርምያስን ታሪክና የተናገራቸውን ትንቢቶች እናገኛለን። በብሉይ ኪዳን ከሚገኙ ነቢያት ሁሉ ስለ ሕይወቱ፥ ስለ አሳለፈው ትግል፥ ስለ ጥርጣሬውና ስለ ደረሰበት ስደት ይበልጥ በዝርዝር የተናገረ ኤርምያስ ነው። የኤርምያስን ሕይወት በምናጠናበት ጊዜ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ስለሚኖር ታላቅነትና በመንፈሳዊ ሕይወቱ ስለበሰለ ክርስቲያን ምንነት የሚኖሩን በርካታ አሳቦች ፈተና ይገጥማቸዋል። ኤርምያስ በእግዚአብሔር አመለካከት ታላቅ ሰው ነበር፤ ነገር ግን ብዙዎቻችን ኤርምያስ ጽኑ እምነት የሌለውና ታላቅ ሊባል የማይችል ሰው እንደሆነ ልናስብ እንችላለን፡- ታላላቅ ሊባሉ የሚችሉ ወንጌላውያንና ሰባኪዎች፥ ብዙ ነፍሳትን ለጌታ የሚማርኩና ሁልጊዜ

ደስተኞች ሆነው እንዲሁም ሰምሮላቸው የሚኖሩ ሰዎች እንደሆኑ የማሰብ ዝንባሌ አለን። ይህ ግን ሁልጊዜ እውነት አይደለም። እግዚአብሔር ታላቅነታችንን የሚለካው ወደ ጌታ ባመጣናቸው በርካታ ሰዎች ምክንያት፥ ወይም ሰዎች በእኛ ደስ በመሰኘታቸው አይደለም። ታላቅነታችን የሚለካው እጅግ አስቸጋሪና አስጨናቂ በሆኑና እግዚአብሔርን ሳይቀር እንድንጠራጠር በሚጋብዙ ሁኔታዎች ውስጥ ለእግዚአብሔር በሚኖረን ታማኝነት ነው። የኤርምያስን ሕይወት በሚገባ ብንመለከት የሚከተሉትን ነገሮች ለማየት እንችላለን፡-

1. የኤርምያስ የሰብከት አገልግሎት በሙሉ ከንቱ ይመስል ነበር። በሚያስተምረው ትምህርት የሚለወጡ ሰዎችን ማግኘት አልቻለም ነበር። ሕዝቡ ከክፋታቸው ተመልሰው በጽድቅ መንገድ ይመላለሱ ዘንድ ሊመራቸው አልቻለም። ይሁን እንጂ ኤርምያስ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዲናገር የሰጠውን መልእክት በታላቅ ብርታት ይናገር ነበር። መልእክቱ የማስጠንቀቂያና የፍርድ መልእክት ነበር። መልእክቱ ሰዎች ሊሰሙት የማይፈልጉት ዓይነት ቢሆንም እንኳ ኤርምያስ ለሕዝቡ ያመጣውን የእግዚአብሔርን መልእክት በታማኝነት ተናገረ። በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ያሰኘው ይህ ታማኝነቱ ነበር።

2. የኤርምያስ ሕይወት በታላቅ መከራ፥ በስደትና በብቸኝነት የተሞላ ነበር። ኤርምያስ ሚስት ለማግባት የነበረው መብት በእግዚአብሔር ታግዶ ነበር። አብዛኛው የአገልግሎት ዘመኑ ሊያገለግላቸው በሞከረ ሰዎች በኩል በሚነሣበት ስደት የተሞላ ነበር። ይህ ነገር ኤርምያስን ብዙ ጊዜ በእጅጉ ተስፋ ያስቈርጠው ነበር። ስለ ሕዝቡ ኃጢአትና ዓመፅ ያውቅ ስለነበር በሕዝቡ ላይ ስለሚመጣው ጥፋት በማልቀሱ ምክንያት «አልቃሻው ነቢይ» ይባል ነበር (ለምሳሌ፡- ኤርምያስ 13፡17)። ኤርምያስ ብቸኝነት በእጅጉ ስላጠቃው ባይወለድ ይሻለው እንደነበር ሲመኝ እናገኘዋለን (ኤርምያስ 20፡13-18)። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔርን በመጠራጠር ይጠይቀው ነበር። ኤርምያስ ከእግዚአብሔር ዕቅድና ዓላማ ጋር ታግሏል፤ ነገር ግን ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር ጥሪ ታማኝ ሆኖአል። እንዲሁም ታላቅ ስደትን ስላስከተለበትና ማንም ሰው ስለማይሰማው አገልግሎቱ ከንቱ የሆነ ቢመስልም የእግዚአብሔርን ቃል ተናግሯል።

3. ኤርምያስ በግል የነበረበት ትግል ከእግዚአብሔርና ከሌሎችም ጋር እውነተኛና ግልጽ ነበር። በሰዎች ፊት «ቅዱስ» በመምሰል፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያካሂደው የነበረውን ውስጣዊ ትግል ለመሰወር አልሞከረም። ይልቁንም በእግዚአብሔር ፊት ነበር። ታግሎ በሚጐዳበት ጊዜም ለእግዚአብሔር ይናገር ነበር። ያደረገውንም ትግል በመጽሐፉ ውስጥ መዝግቦታል። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ውስጥ ስላለው ትግል በእግዚአብሔርና በሌሎች ፊት ግልጽ መሆን የታላቅነት እንጂ የደካማነት ምልክት አይደለም። ቅዱስ የመምሰል ግብዝነትን ከማሳየት የመታቀብና ፍጹም ታማኝነትን የማሳየት ምልክት ነው።

2ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ብዙ ጊዜ ስለተዋጣለት የእግዚአብሔር ሰው ካለን አስተሳሰብ የኤርምያስ ሕይወት የሚለየው እንዴት ነው? ለ) አንዳንድ ጊዜ አገልግሎትህ ከንቱ እንደሆነ በማሰብ፥ የእግዚአብሔርን ዕቅድና ዓላማ በጥርጣሬ የጠየቅከበትን መንገድ ግለጽ። ሐ) ከኤርምያስ ሕይወት ስለ መሪነት ምን እንማራለን?

የትንቢተ ኤርምያስ ጸሐፊ

ትንቢተ ኤርምያስን የጻፈው የኬልቅያስ ልጅ ኤርምያስ ራሱ ነው። ኤርምያስ ያደገው የይሁዳ ዋና ከተማ ከሆነችው ከኢየሩሳሌም 5 ኪሎ ሜትር ያህል ወጣ ብላ በምትገኝ ዓናቶት በተባለች ትንሽ ከተማ ነበር። ወላጆቹ ከካህኑ ከአሮን የዘር ግንድ የመጡ ስለነበሩ ኤርምያስ ካህን ነበር። ኤርምያስ የተወለደው እግዚአብሔርን ይፈሩ ከነበሩ የአይሁድ ነገሥታት የመጨረሻው ኢዮስያስ በተወለደበት ዘመን ገደማ በ650 ዓ.ዓ. ነበር። ኢዮስያስ በይሁዳ ሁሉ የመንፈሳዊ ተሐድሶ እንቅስቃሴ ከጀመረ (628 ዓ.ዓ.) ከአንድ ዓመት በኋላ (በ627 ዓ.ዓ.) ኤርምያስ የነቢይነት ጥሪውን ከእግዚአብሔር ተቀበለ። የኤርምያስ የነቢይነት ጥሪ ከኢሳያይስና ከሕዝቅኤል ጥሪ ጋር የሚመሳሰል አልነበረም። ታላቅ የሆነ የእግዚአብሔር ራእይ ስላልነበረ የተለየ ትርኢት ያዘለ አልነበረም። እግዚአብሔር መሪዎችን ወደ አገልግሎት ለመጥራት የሚጠቀምበት ዘዴ አንድ ዓይነት አይደለም፤ ነገር ግን ኤርምያስ ለሕዝቡ የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ሆኖ እንዲያገለግል በእግዚአብሔር መጠራቱን ያውቅ ነበር። ኤርምያስ ነቢይ ለመሆን ብቁ እንዳይደለ ቢሰማውም እንኳ እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን

መፍራት እንደሌለበት በመናገር፥ እግዚአብሔር ጥሪውን አረጋገጠለት። መልእክቱም የመልካም ተስፋ ቃል ኪዳን ያዘለ ሳይሆን የጥፋትና የፍርድ መልእክት እንደሆነ አስጠነቀቀው። ሕዝቡም መልእክቱን እንደማይሰሙና ኤርምያስን እንደሚቃወሙት በመንገር አስጠነቀቀው፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለሚሆን፥ ሕዝቡ ቢቃወሙትም እንደማያሸንፉት ተስፋ ሰጠው።

3ኛ ጥያቄ፥ ኤርምያስ 1 አንብብ። ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉ በኤርምያስ ጥሪ ውስጥ የሚገኙትን ትምህርቶች ማስታወስና መታዘዝ የሚያስፈልጋቸው እንዴት ነው? ለ) ከእግዚአብሔር የተቀበልከው ምን ጥሪ አለህ? እግዚአብሔር በሕይወትህ እንድታከናውነው የሚፈልገው ምንድን ነው?

ንጉሥ ኢዮስያስ በይሁዳ ባካሄደው መንፈሳዊ ተሐድሶ ውስጥ የኤርምያስ ድርሻ ምን እንደነበር የምናውቀው ነገር የለም። ኤርምያስ የተቀረጹ ምስሎች ሁሉ እየተደመሰሱ በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚካሄድ አምልኮ ሲታደስ በተመለከተ ጊዜ እጅግ እንደተደሰተ መገመት እንችላለን። ከዚያ በኋላ ግን ንጉሥ ኢዮስያስ በጦርነት በተገደለ ጊዜ ኤርምያስ እጅግ እንዳዘነ እንመለከታለን (2ኛ ዜና 35፡25 ተመልከት)። ኤርምያስ ስለ ኢየሩሳሌምና ይሁዳ መጥፋት የተነበየውና ሕዝቡ ንስሐ እንዲገቡ አጥብቆ መለመን የጀመረው ከኢዮስያስ ሞት በኋላ ነበር። ሕዝቡ አሻፈረኝ ብለው ወደ ጣዖት አምልኮ በተመለሱ ጊዜ ከእግዚአብሔር የሚመጣው ጥፋት የማይቀር መሆኑን ኤርምያስ አወቀ። ኤርምያስ ስለ ሕዝቡ እንዲጸልይ እንኳ እግዚአብሔር አልፈቀደም ነበር (ኤርምያስ 7፡17፤ 11፡14)። ኤርምያስ ሕዝቡ ሊጠፉ እንደቀረበ በመናገር መሪዎች እጃቸውን ለባቢሎናውያን እንዲሰጡ መጠየቅ ሲጀምር የተለያየ ጥቃትና ስደት ደረሰበት። የኤርምያስ የቅርብ ወዳጅ፥ መልእክቱን የጻፈለት ጸሐፊው ባሮክ ነበር። የትንቢቱን የመጀመሪያ ቅጅ ንጉሡ አቃጠለው (ኤርምያስ 36፡1-28)። ኤርምያስ ትንቢቶቹን እንደገና ጻፋቸው። ኢየሩሳሌም ከተደመሰሰችና ሕዝቡ ተማርከው ከሄዱ በኋላ እንኳ አይሁድ በይሁዳ እንዲሰፍሩና ሰላማዊ ኑሮ እንዲኖሩ የሚመክራቸውን ኤርምያስን መስማት እምቢ አሉ። ይልቁንም ኤርምያስን

አፍነው ወደ ግብፅ ወሰዱት። የአይሁድ አፈ ታሪክ እንደሚናገረው፥ ኤርምያስን በግብጽ ምድር በድንጋይ ወግረው የገደሉት አይሁድ ናቸው (ዕብራውያን 11:37)።

የኤርምያስ የነቢይነት አገልግሎት የተጀመረው በ626 ዓ.ዓ. ሲሆን፥ የተጠቃለለው ደግሞ ከ586 ዓ.ዓ. በኋላ ነው። ይህ ማለት ኤርምያስ እግዚአብሔርን በታማኝነት ያገለገለው ከ40 ዓመታት በላይ ነው ማለት ነው።

የኤርምያስ ሕይወት በሁለት ዐበይት ባሕርያት ሊለይ ይችላል፤ የመጀመሪያው፥ ርኅራኄ ነው። የኤርምያስ መልእክት የጥፋት መልእክት የነበረ ቢሆንም፥ በደረሰበት ስደት ምክንያት መራር አልሆነም ወይም የሕዝቡን ሥቃይና መከራ አይቶ ርኅራኄ አልጐደለውም ነበር። ኤርምያስ አልቃሻው ነቢይ በመባል ይታወቅ እንደነበር ቀደም ሲል ጠቅሰናል፤ ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ በመጽሐፉ ውስጥ በአጠቃላይ የሕዝቡን ኃጢአትና የሚደርስባቸውን ጥፋት በሚመለከት ስለ ውስጣዊ ሥቃዩና ኃዘኑ ማንበብ ስለሚቻል ነው። (ለምሳሌ:- ኤርምያስ 8:21-9:1)። እንደ እውነቱ ከሆነ ከኢየሩሳሌም መደምሰስ በኋላ ኤርምያስ የጻፈው ሰቆቃወ ኤርምያስ ለሕዝቡ ያለቀሰው ልቅሶ ወይም ሙሾ የተመዘገበበት ነው።

4ኛ ጥያቄ፥ የሚከተሉትን ጥቅሶች በመመልከት ኤርምያስ የተጋፈጣቸውን ችግሮች ዘርዝር:- ኤርምያስ 16:1-4፤ 20:1-3፤ 26:11-15፤ 28:10-11፤ 36:19፥ 26፤ 37:11-15፤ 38:5-6።

ሁለተኛ፥ ኤርምያስ በጣም ድፍረትና ብርታታ የነበረው ሰው ነበር። ብዙ ጊዜ ተስፋ የቆረጠ ቢሆንም፥ የነቢይነት አገልግሎቱን ግን አቋርጦ አያውቅም። ኤርምያስ ከሌሎቹ ነቢያት ሁሉ የላቀ ስደት የደረሰበት ነቢይ ነበር። በቤተ መቅደስ ተይዞ ለአንድ ምሽት በሰንሰለት ታስሮአል። ስለ ቤተ መቅደሱ መደምሰስ በተናገረ ጊዜ ካህናትና ሐሰተኞች ነቢያት ሊገድሉት ሞክረው ነበር። (አርዮ የተባለ ሌላ ነቢይ የተገደለው በዚህ ጊዜ ነበር [ኤርምያስ 26:20-23])። ትምህርቱን ይቃወሙ በነበሩ ሐሰተኞች

ነቢያት የማያቋርጥ ጥቃት ደርሶበታል። ኤርምያስ በተወለደበት ከተማ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ሳይቀሩ ተቃውመውት ሊገድሉት ዝተውበት ነበር (ኤርምያስ 11፡21-23)። የመጀመሪያው መጽሐፉ የተቃጠለ ሲሆን፥ ንጉሡም እርሱንና ጸሐፊውን ባሮክን ለመያዝ ሞክሮ ነበር። ከባቢሎን ጋር በተደረጉት የመጨረሻ ጦርነቶች በንጉሡ ላይ ዓመፅ አነሣሥተሃል ተብሎ ተከሶአል፤ ተገርፎአል፤ በእስር ቤትም ተጥሏል። በኋላ ደግሞ ንጉሥ ሴዴቅያስ በግዞት አስቀምጦታል። ሴዴቅያስ ሕዝቡን ደስ ለማሰኘት ብሎ ኤርምያስን የሚያሰጥም ሞታ ባለበት ጕድጓድ ውስጥ እንዲጣል አድርጓል። በኋላ አንድ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ አዳነውና እንደገና በግዞት እንዲቆይ አደረገው። ኤርምያስ የተራበ፥ ወደ እስር የተጣለ፥ የተገረፈና ብዙ ጊዜ ሕይወቱ ለሞት አደጋ የተጋለጠ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር የሰጠውን መልእክት በታማኝነት ከማስተላለፍ ወደኋላ አላለም።

5ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ርኅራኄና ድፍረት በዚህ ዘመን ለሚኖሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እጅግ አስፈላጊ ባሕርያት የሆኑት ለምንድን ነው? ለ) እነዚህ ባሕርያት በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙ ጊዜ ይታያሉን? ካልታዩስ ለምን? ሐ) እነዚህ ባሕርያት በሕይወትህ ይታያሉን? ሕይወትህን በመመርመር እነዚህን ባሕርያት በሕይወትህ እንዲጐለብቱልህ እግዚአብሔርን በጸሎት ለምነው።

በዚህ ጊዜ በይሁዳ የሚያገለግል ነቢይ ኤርምያስ ብቻ አልነበረም። ኤርምያስ አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት ሶፎንያስ ያገለግል ነበር። ኤርምያስ ባገለገለበት ዘመን በይሁዳ ያገለግሉ የነበሩ ነቢያት ዕንባቆምና ምናልባት አብድዩ ነበሩ። በኤርምያስ ዘመን መጨረሻ ገደማ ሕዝቅኤልም ያገለግል ነበር፤ ነገር ግን የሚኖረው በባቢሎን በምርኮ ነበር።

የኤርምያስ ታሪካዊ ሥረ- መሠረት

ኤርምያስ የተወለደውና የመጀመሪያዎቹን የሕይወት ዘመኑን የኖረው የይሁዳ ሕዝብ የመጨረሻዎቹን የሰላም ዓመታት ባሳለፉበት ጊዜ ነበር። ኤርምያስ ከተወለደበት ከ650 ዓ.ዓ. ጀምሮ ኢዮስያስ እስከሞተበት እስከ 609 ዓ.ዓ. በይሁዳ ፖለቲካዊ ሰላምና ሃይማኖታዊ መነቃቃት ነበር። ንጉሥ ኢዮስያስ እግዚአብሔርን በመፍራት መንፈሳዊ ተሐድሶንና መነቃቃትን ወደ ይሁዳ ለማምጣት ሞክሯል። ከፖለቲካ አንጻር ጊዜው

ሰላም የሰፈነበት ነበር። የይሁዳ ጠላት የነበረችው አሦር በሥልጣን እጅግ እያሽቆለቆለች የመጣችበትና ተከታይዋ የዓለም ኃያል መንግሥት የሆነችው ባቢሎን ደግሞ ገና ያልተጠናከረችበት ወቅት ነበር፤ ስለዚህ ይሁዳ ብቻዋን ቀርታ ነበር። ኤርምያስ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ሁሉ ነቢይ ሆኖ ያገለገለ ቢሆንም፥ ስለ አገልግሎቱ ብዙ የምናውቀው ነገር የለም።

በ612 ዓ.ዓ. ነገሮች ተለወጡ። አሦር የሚቀጥለው የዓለም ኃያል መንግሥት በሆነችው በባቢሎን ተሸነፈች። በ609 ዓ.ዓ. ግብፆች ከባቢሎን ጋር በተደረገ የመጨረሻ ጦርነት ከአሦር ጋር ለመተባበር በይሁዳ በኩል አለፉ። ንጉሥ ኢዮስያስ ግብፆች አገሩን እንደመተላለፊያ እንዲጠቀሙ ከመፍቀድ ይልቅ ከግብፆች ጋር ለመዋጋት ወጣ። ይህ ጦርነት እርሱን የሚመለከት ስላልነበረ የሞኝነት ሥራ ሠራ። በዚህ ጦርነት ንጉሥ ኢዮስያስ ተገደለ። በንጉሡ ሞት የይሁዳ ሕዝብና መንግሥት ወዲያውኑ ተብረከረኩ። ኢዮስያስ ከተገደለበት ከ609 ዓ.ዓ. ጀምሮ የይሁዳ ሕዝብ እስከተመቱበት እስከ 586 ዓ.ዓ. ድረስ የነበረው ወቅት በይሁዳ ታሪክ ውስጥ እጅግ አስጨናቂ ጊዜ ነበር።

የኢዮስያስ ታላቅ ልጅ ኢዮአካዝ ጥቂት ወራት ብቻ ከነገሠ በኋላ (609 ዓ.ዓ.) በግብፅ ንጉሥ ተማርኮ ተወሰደ። ይህ ንጉሥ በምርኮ ከተወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ኤርምያስ እንደወዳጅ የሆነ ንጉሥ ስላልገጠመው ስደት ይደርስበት ጀመር።

የኢዮስያስ ሁለተኛ ልጅ ኢዮአቄም የሚቀጥለው ንጉሥ በመሆን ከ609-598 ዓ.ዓ. ድረስ ገዛ። ኢዮአቄም እንደ አባቱ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ስላልነበረ ኢዮስያስ አስገኝቶ የነበረውን መንፈሳዊ ተሐድሶ በሙሉ ወዲያውኑ ደብዛው እንዲጠፋ አደረገ። የጣዖት አምልኮ በይሁዳ ሁሉ ተስፋፋ። አብዛኛው የኤርምያስ አገልግሎት የተካሄደው በዚህ ጊዜ ነበር። ኤርምያስ ሕዝቡ በፍጥነት ወደ ጣዖት አምልኮ መመለሳቸውን በማየቱ የይሁዳ ጥፋት በደጅ መሆኑን አውቆ ነበር። እነዚህን የጣዖት አምልኮ በግልጽ በመቃወሙ፥ ከኢዮአቄም ዘንድ ከፍተኛ ጥላቻን አተረፈ። በ606 ዓ.ዓ. ኃያል የሆነው የባቢሎን መንግሥት ይሁዳን ማጥቃት ጀመረ። ጦርነቱ እጅግ ከፍተኛ እንኳ ባይሆንም፥ ኢዮአቄም የባቢሎን ተገዥ ሆነ። ዳንኤልና ሌሎች ንጉሣውያን ቤተሰቦች ተማርከው

የሄዱት በዚህ ጊዜ ነበር። በ598 ዓ.ዓ. ኢዮአቄም በባቢሎን ላይ ለማመፅ ወሰነ። ባቢሎን ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም በመምጣት ጥቃት አካሄደችና ይሁዳን ድል አደረገቻት፤ ኢዮአቄምም ሞተ። ንጉሥ ናቡከደነፆር የኢዮአቄምን ልጅ ኢኮንያንን ማርኮ ወደ ባቢሎን ወሰደው። እዚያም ቀሪውን የሕይወት ዘመኑን አሳለፈ። በተጨማሪ ከይሁዳ ታዋቂ ሰዎች አሥር ሺህ ያህሉን ማርኮ ወደ ባቢሎን አፈለሳቸው። በዚህ ምርኮ ከተወሰዱት መካከል ሕዝቅኤልም ይገኝበታል። በይሁዳ የቀሩት ያልተማሩና ድሀ ሰዎች ብቻ ነበሩ።

የመጨረሻው የይሁዳ ንጉሥ የኢዮስያስ ልጅ የኢዮአቄም ወንድም ሴዴቅያስ ነበር። ይህ ንጉሥ ከኤርምያስ ጋር የነበረው ግንኙነት ተለዋዋጭ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ኤርምያስ የሚለውን ይሰማና ይረዳው ነበር፤ ዳሩ ግን የኤርምያስን ምክር ለመታዘዝ ፈቃደኛ አልነበረም። በሌላ ጊዜ ደግሞ በኤርምያስ ላይ ስደት እንዲነሣ አደረገ። በ586 ዓ.ዓ. በባቢሎን ላይ በማመፁ፥ ባቢሎናውያን በይሁዳ ላይ የነበራቸው ትዕግሥት ተሟጠጠ። የባቢሎን ጦር የሴዴቅያስን ልጆች ገደለ፤ ሴዴቅያስን አሳወረና ማረከው። የኢየሩሳሌምን ከተማ ቅጥሮች፥ ሕንጻዎችና ቤተ መቅደሱን አፈራረሰ። ኤርምያስ ይህንን ሁሉ ሞትና ጥፋት በጥልቅ ኃዘን ተመለከተ። ዳሩ ግን ከ70 ዓመታት በኋላ የይሁዳ ሕዝብ ከምርኮ በመመለስ ቤተ መቅደሱንና ቅጥሩን እንደገና እንደሚሠሩ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቶ ስለነበር ይህ ነገር ጊዜያዊ መሆኑን ያውቅ ነበር (ኤርምያስ 25፡10-12፤ 29፡10)።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰባ ዓመታት ምርኮ በተለያዩ መንገዶች ሊቀርብ ይችላል። የፖለቲካ ምርኮው የተጀመረው የመጀመሪያዎቹ ምርኮኞች ወደ ባቢሎን በተወሰዱበት በ605 ዓ.ዓ. ሲሆን፥ የተፈጸመው ደግሞ አይሁድ ወደ ይሁዳ እንዲመለሱ በተፈቀደላቸው በ538 ዓ.ዓ. ነበር። የሃይማኖት ምርኮው ደግሞ የተጀመረው ቤተ መቅደሱ በተደመሰሰበት በ586 ዓ.ዓ. ሲሆን፥ የተጠቃለለው ደግሞ ቤተ መቅደሱ እንደገና በተሠራበት በ516 ዓ.ዓ. ነበር።

በኤርምያስ ሕይወት ውስጥ ሊጠቀሱ የሚገባቸው ዋና ዋና ዓመታት፡-

650 ዓ.ዓ. - ኤርምያስ ተወለደ፤

640 ዓ.ዓ. - ኢዮስያስ ነገሠ፤

628 ዓ.ዓ. - ኢዮስያስ መንፈሳዊ ተሐድሶ ጀመረ፤

627 ዓ.ዓ. - ኤርምያስ የነቢይነት ጥሪውን ከእግዚአብሔር ተቀበለ፤

612 ዓ.ዓ. - አሦር በባቢሎን እጅ ወደቀች፤

609 ዓ.ዓ. - ኢዮስያስ በጦርነት ተገደለ፤

605 ዓ.ዓ. - ባቢሎን ይሁዳን አስገበረች፤ ዳንኤል በምርኮ ተወሰደ፤

597 ዓ.ዓ. - ባቢሎን ኢየሩሳሌምን አሸነፈች፤ ሕዝቅኤልና አሥር ሺህ ሰዎች ተማረኩ፤

586 ዓ.ዓ. - ባቢሎን ኢየሩሳሌምን ደመሰሰች።

ትንቢተ ኤርምያስ

ትንቢተ ኤርምያስ የተሰየመው በጸሐፊው በነቢዩ ኤርምያስ ስም ነው (ኤርምያስ 1፡1)። መጽሐፉ እንዴት እንደተጻፈ ኤርምያስ የተለያዩ ፍንጮችን ይሰጠናል። ከመጽሐፉ የተወሰኑ ክፍሎች የተጻፉት ኤርምያስ ለ20 ዓመታት ከተነበየ በኋላ፥ በ605 ዓ.ዓ. መሆኑን እናውቃለን። መጽሐፉን እንዲጽፍ እግዚአብሔር ኤርምያስን አዘዘው (ኤርምያስ 36፡1-3 ተመልከት)። መጽሐፉን የጻፈው ኤርምያስ ራሱ አልነበረም። መጽሐፉን ለማስጻፍ ጸሐፊውን ባሮክን ተጠቀመበት (ኤርምያስ 36፡4)። ንጉሥ ኢዮአቄም የመጀመሪያውን ቅጅ ባነበበ ጊዜ አቃጠለው፤ ስለዚህ ኤርምያስ መጽሐፉን ለሁለተኛ ጊዜ ጻፈው። ይህ ትንቢት ዛሬ በእጃችን በሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ክፍል ሳይሆን አይቀርም (ኤርምያስ 36፡32)።

አንዳንድ ምሁራን ኤርምያስ የጻፈው የመጀመሪያ መጽሐፉ ከትንቢተ ኤርምያስ የመጀመሪያ ክፍል ማለት ከምዕራፍ 1-25 ጋር ተመሳሳይ ነው ይላሉ። ይህንንም የኤርምያስ የመጀመሪያ የትንቢት መጽሐፍ ብለው የሚጠሩት ሲሆን፥ በዚህ ክፍል ያለው አብዛኛው ንግግር ኤርምያስ ራሱ እንደተናገረው ተደርጎ የተጻፈ ነው። ቆይቶ ሌሎች ሁለት የትንቢተ ኤርምያስ ክፍሎች ተጨመሩ። ኤርምያስ 30-31 የኤርምያስ ሁለተኛ መጽሐፍ ተብሎ ሲጠራ፥ ኤርምያስ 46-51 ደግሞ ሦስተኛ መጽሐፍ ተብሎ ይጠራል። በኋላ በሌሎች ሦስት ክፍሎች ባሮክ ወይም ሌላ ሰው

ስለ ኤርምያስ ሕይወት የሚናገሩ ታሪኮችን እንደጨመረ ይገመታል፤ እነርሱም፡- ኤርምያስ 26-29፤ 32-45 ና 51፡59-52፡34 ናቸው።

ትንቢተ ኤርምያስ የተጻፈው በጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት ሳይሆን በተለየ መንገድ ነው። ቁጥሉ የትንቢተ ኤርምያስ ምዕራፎች በጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት ተገልጸዋል፡-

1. በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት የተጻፉ ምዕራፎች፡- ኤርምያስ 1-7፡15፥
2. በኢዮአካዝ ዘመነ መንግሥት የተጻፉ ምዕራፎች፡- ኤርምያስ 22፡10-12፥
3. በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት የተጻፉ ምዕራፎች፡- ኤርምያስ 26፤ 7፡16-20፡18፤ 25፤ ምዕራፍ 35 ና 36፤ 45-46፡12፤ ምዕራፍ 47-49፥
4. በኢኮንያን ዘመነ መንግሥት የተጻፉ ምዕራፎች፡- ኤርምያስ 22፡1-9፥ 13-20፤ 23፥
5. በሴዴቅያስ ዘመነ መንግሥት የተጻፉ ምዕራፎች፡- ኤርምያስ 21፤ 24፤ 27-34፤ 37-39፤ 46፡13-28፤ 50-51፥
6. ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ የተጻፉ ምዕራፎች፡- ኤርምያስ 40-44፤ 52 ናቸው።

የማይመስል ቢሆንም እንኳ የብሉይ ኪዳን ረጅሙ መጽሐፍ ትንቢተ ኤርምያስ ነው። ኤርምያስ መልእክቱ ኃይል እንዲኖረው ለማድረግ ግጥምን ከስድ ንባብ ጋር አቀናጅቶ ያቀረበ፥ የሥነ-ጽሑፍ ጥበብ የነበረው ሰው ነበር። በትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ አራት ዓይነት ዐበይት ስብከቶችን እናገኛለን፡-

ሀ. የይሁዳን ኃጢአት የሚገልጹ ስብከቶች (ለምሳሌ፡- ኤርምያስ 5-9)፡- ኤርምያስ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ትተው ጣዖታትን ስላመለኩና በሲና ተራራ ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ስላፈረሱ ይገሥጻቸዋል።

ለ. በይሁዳ ላይ የሚመጣውን ፍርድ የሚያመለክቱ ስብከቶች፡- ይህኛው ከሁሉም ዓይነት ስብከት ይልቅ የተለመደ የስብከት

ዓይነት ነው። በኢየሩሳሌም ላይ ሊመጣ ስላለው ጥፋትና ስለ ሕዝቡ መማረክ ይናገራል። በቃል ኪዳኑ ውስጥ የነበሩት መርገሞች እንዴት እንደተፈጸሙ ያመለክታል (ዘዳግም 28፡15-68ን ከኤርምያስ 11፡8 ጋር አወዳድር)።

ሐ. ለሕዝቡ ትምህርት የሚሰጡ ስብከቶች፡- እነዚህ ሕዝቡ መንገዳቸውን እንዲለውጡና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ የሚለምኑ ወይም እግዚአብሔር በአሕዛብ አማልክትና ጣዖታት ላይ ያለውን ሥልጣንና ታላቅነት የሚያሳዩ ስብከቶች ናቸው።

መ. የመጽናኛ ስብከቶች፡- እንደ ትንቢተ ኢሳይያስ በተለየ መንገድ ሕዝቡን የሚያጽናኑ ብዙ ስብከቶች አላቀፈም። ይሁን እንጂ ኤርምያስ ለእግዚአብሔር ባላቸው ታማኝነት ጸንተው የሚቆዩ ጥቂቶችን ያጽናናል። ኤርምያስ ከሰባ ዓመታት በኋላ ከምርኮ እንደሚመለሱ ለሕዝቡ ተናገረ። እንዲሁም አንድ ቀን እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ስለሚያደርገው «አዲስ ቃል ኪዳን» ተናግሯል (ኤርምያስ 29፡10-11፤ 31፡31-34)።

6ኛ ጥያቄ፡ ሀ) እነዚህ አራት ዓይነት ስብከቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሰበኩ የሚችሉባቸውን መንገዶች ግለጽ። ለ) በብዛት የሚሰበከው የትኛው ስብከት ነው? ለምን? ሐ) ሁሉም ዓይነት ስብከት ይሰበክ ዘንድ ስብከቶቻችንን ሚዛናዊ አድርጎ ማቅረብ አስፈላጊ ነውን? ለምን?

እንደ ሕዝቅኤል ሁሉ ኤርምያስም መልእክቱን ለማጠናከር በርካታ ምሳሌያዊ ተግባራትን አከናውኖአል፡- ከተልባ እግር የተሠራች የተበላሸችውን መታጠቂያ (ኤርምያስ 13፡1-11)፡ የተሰባበረች ገንቦ (ኤርምያስ 19፡1-12)፡ የእስራት ቀንበርን (ኤርምያስ 27)፡ የተሸሸጉ ድንጋዮችን (ኤርምያስ 43፡8-13)፡ ሚስት ከማግባትና ልጆችን ከመውለድ መታቀብን (ኤርምያስ 16፡1-4)፡ ቀብርና ሠርግ ወዳለበት ቤት አለመግባት (ኤርምያስ 16፡5-9)፡ በተወለደበት ከተማ መሬት መግዛትን (ኤርምያስ 32፡6-15) እና የሸክላ ሥራን (ኤርምያስ 18፡1-10) ተጠቅሞአል።

የትንቢተ ኤርምያስ አስተዋጽኦ

የትንቢተ ኤርምያስን አስተዋጽኦ ማዘጋጀት አስቸጋሪ ነው። በአጠቃላይ በመጽሐፉ ውስጥ የሚታይ ግልጽ የሆነ ዐቢይ አሳብ የለም። እያንዳንዱ ምዕራፍ ከሌሎች ምዕራፎች የተለየ ትምህርት የሚሰጥ ይመስላል። የትንቢተ ኤርምያስን አስተዋጽኦ ማዘጋጀት አስቸጋሪ የሆነበት ሌላው ምክንያት በጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት አለመቅረቡ ነው።

ቀጥሎ አንድ የትንቢተ ኤርምያስ አስተዋጽኦ ቀርቧል፡-

1. የኤርምያስ ለነቢይነት መጠራት (ኤርምያስ 1)፥
2. ኤርምያስ ለይሁዳ ሕዝብ ያስተላለፈው ማስጠንቀቂያና ማበረታቻ (ኤርምያስ 2-35)፥
3. በኤርምያስ ላይ የደረሰው ስደትና መከራ (ኤምያስ 36-38)፥
4. የኢየሩሳሌም ውድቀትና ያስከተለው ውጤት (ኤርምያስ 39-45)፥
5. በአሕዛብ ላይ የተላለፉ የፍርድ ትንቢቶች (ኤርምያስ 46-51)፥
6. ታሪካዊ መደምደሚያ (ኤርምያስ 52)።

> 7ኛ ጥያቄ፥ ስለ ኤርምያስ ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አንብብ። በዚያ ከተጠቀሱት እውነቶች መካከል እጅግ ጠቃሚ የሆኑትን ዘርዝር።

የትንቢተ ኤርምያስ ዓላማ

ትንቢተ ኤርምያስ የተጻፈው ስለ ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎች ነበር፤ አንደኛ፥ የይሁዳ ሕዝብ ለምን እንደተማረኩ ለመግለጽ ነበር። ይህ ክፍል እግዚአብሔር ለሕዝቡ የነበረውን የመጨረሻ መልእክት የሚነግረን ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ራሱ ለመመለስ የሞከረበት፥ ሕዝቡ በእግዚአብሔርና በሕጉ ላይ በማመፃቸው ምክንያት የሚደርስባቸውን ነገር በማሳየት የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ ሁሉ የምናይበት ነው። ሕዝቡ የነበረበትን መንፈሳዊ ሁኔታ፥ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ አሻፈረኝ ማለታቸውንና በዚህ ምክንያት የደረሰባቸውን የምርኮ ፍርድ ያሳያል።

8ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ሰዎች እግዚአብሔር ለምን እንደሚቀጣቸው ማወቅ ያለባቸው ለምንድን ነው? ለ) ይህ ነገር በቤተ ክርስቲያንህ የሚከናወነው እንዴት ነው?

የትንቢተ ኤርምያስ ሁለተኛ ዓላማ የነቢዩ ኤርምያስን ሕይወትና ያለፈበትን ትግል ማሳየት ነበር። የኤርምያስ ሕይወት ተቀባይነት በማይገኝበት መሃከል የታማኝነት አመራር ምሳሌ ይሆን ዘንድ ቀርቧል። ኤርምያስ ሥራው ምንም ለውጥ የሚያመጣ በማይመስልበት ሁኔታ እንኳ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ የሚኖር ሰው ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። እግዚአብሔርን እንከተላለን በሚሉ ሰዎች አማካይነት ስደትና ተቃውሞ ቢገጥመውም እንኳ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ቆረጠ። ይህም ማለት ኤርምያስ አልታገለም፤ አገልግሎቱን ለማቋረጥ አልፈለገም ማለት አይደለም። ኤርምያስ እግዚአብሔርን በፍጹም ተጠራጥሮ አያውቅም ማለትም አይደለም። በትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ እነዚህን ትግሎች እናያለን፤ ነገር ግን ኤርምያስ ለራሱ የሚመቸውን ነገር በመምረጥ የተጠራበትን አገልግሎት አላቋረጠም።

9ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህንን ትምህርት በሕይወታችን መማር የሚያስፈልገን ለምንድን ነው? ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ የኤርምያስን ዓይነት ተመሳሳይ ችግር የገጠማቸው አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በምሳሌነት ጥቀስ።

ኤርምያስ ብዙ ሚስዮናውያንና ወንጌላውያን ከሙስሊሞችና ለማመን ፈቃደኞች ካልሆኑ ሰዎች ጋር በሚሠሩበት ጊዜ ለሚገጥሟቸው ችግሮች ጥሩ ምሳሌ ነው። ብዙ ሚሲዮናውያን በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ በአንድ አካባቢ ሠርተው አንድም ሰው እንኳ ወደ ክርስቶስ ሳያመጡ አልፈዋል። እነዚህ ሰዎች አልሠመረላቸውም ማለት ነውን? ለዚህ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ ለመስጠት እንፈተን ይሆናል። እግዚአብሔር ግን እንዲሠሩ ያዘዛቸውን ነገሮች በታማኝነት እስከሠሩ ድረስ ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ አሉታዊ ነው። በእግዚአብሔር አመለካከት ታላቅነት ማለት በአገልግሎታችን የተዋጣልን ለመሆን መቻል ነው በሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ መጠመድ የለብንም።

በትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ትምህርቶች

1. ኤርምያስ ስለ እግዚአብሔር ብዙ ያስተምረናል። እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ እንደሚቆጣጠርና እርሱ የመጨረሻው ባለሥልጣን እንደሆነ ያስተምረናል። እግዚአብሔር የሕያዋን ነገሮች ሁሉ ፈጣሪ ነው (ኤርምያስ 32:27፤ 48:15፤ 51:57)። እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ማድረግ ይችላል፤ (ኤርምያስ 32:17)። እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ነው፤ ነገር ግን ኃጢአት የሚያደርጉትን ሁሉ የሚቀጣ አምላክም ነው (ኤርምያስ 32:18)። እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ እንደየሥራቸው ይከፍላቸዋል። የዓለምን ሕዝቦች ሁሉ የሚቆጣጠርና በላያቸው ላይ ፍርድን የሚያመጣው እግዚአብሔር ነው (ኤርምያስ 5:15፤ 46-51)።

10ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ታላቅነትና ባሕርይ ትክክለኛ አመለካከት እንዲኖራቸው የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? ለ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉት አባላት በሙሉ ስለ እግዚአብሔር እውነተኛውን ነገር እንዲያውቁ ስለ ባሕርዩ ልታስተምር የምትችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

2. ትንቢተ ኤርምያስ እግዚአብሔር ሕዝቦቹን በሚመለከት ስላለው መመሪያ ያስተምረናል (ኤርምያስ 18:7-11)። የትንቢተ ኤርምያስ የመጨረሻ ክፍል (46-51) በይሁዳ ላይ ጥቃት በፈጸሙ መንግሥታት ላይ ስለሚመጣ ፍርድ የሚናገር ነው። እግዚአብሔር በራሱ ሕዝብ ላይ ስላደረሱት ነገር ፈረደባቸው። አንዳንዶቹ ትንቢቶች ወዲያውኑ ሲፈጸሙ እናያለን፤ ሌሎች ደግሞ ለመፈጸም ብዙ ዓመታት ወስደዋል። አሕዛብ የሚፈረድባቸው መቼ እንደሆነ የሚወስነው እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ እግዚአብሔር ከእነርሱ በላይ ስለሆነ ደግሞ ሕዝቦች ያንን ፍርድ ሊቋቋሙት አይችሉም። አንድ ሕዝብ ክፉ ከሆነ እግዚአብሔር ይፈርድበታል። ነገር ግን አንድ ሕዝብ መልካም ከሆነ ወይም ከክፉ ሥራው ንስሐ ከገባ፥ እግዚአብሔር ያንን ሕዝብ ያድናል። እግዚአብሔር በአሕዛብ ሁሉ ላይ ሉዓላዊ ስለሆነ ስለፈጸሙት ክፉ ተግባር ይፈርድባቸዋል። ብዙ ጊዜ መንግሥታትና ሕዝቦች ክፉ እየሠሩ ያልተቀጡ ቢመስልም፥ እግዚአብሔር ግን በራሱ ጊዜ ይቀጣቸዋል።

11ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በዓለማችን ላይ ጨቋኝ በሆኑ መንግሥታት ሥር ለሚኖሩ በርካታ ክርስቲያኖች ይህ ጉዳይ ማበረታቻ የሚሆነው እንዴት ነው? ለ) መንግሥት ክፉና ጨካኝ በሚሆንበት ወቅት ክርስቲያኖች ምን ማድረግ አለባቸው?

3. ትንቢተ ኤርምያስ ስለ ሐሰተኞች አስተማሪዎችና ነቢያት ብዙ ነገር ይናገራል (ኤርምያስ 14:11-16፤ 23:9-40፤ 28:1-17)። የኤርምያስ ቀንደኛ ጠላቶች የዘመኑ የሃይማኖት መሪዎች ነበሩ። ካህናቱ ኤርምያስን ብዙ ጊዜ ይቃወሙትና ንጉሡ እንዲገድለው ይጠይቁ ነበር፤ ዳሩ ግን ከእነዚህም የሚብሰው በእግዚአብሔር ስም እናስተምራለን እያሉ ሕዝቡን ወደ ክሕደት ይመሩ የነበሩ የሐሰተኞች ነቢያት ጉዳይ ነበር። ኤርምያስ ሊመጣ ስላለው ጥፋት ለሕዝቡ በመንገር ንስሐ እንዲገቡ በሚያስተምርበት ጊዜ ሐሰተኞች ነቢያት ግን ሕዝቡ በግማሽ ልቡ በሚፈጽመው አምልኮ እንዲቀጥል በማበረታታት እግዚአብሔር ብልጽግና፥ ሰላምና በጠላቶቻቸውም ላይ ድልን እንደሚሰጣቸው እንደተናገረ አድርገው ያቀርቡ ነበር። እነዚህ ሐሰተኞች ነቢያት ብዙ ከመሆናቸውም መልእክታቸውም ምንም ሕዝቡን እምብዛም የማያስጨንቅና በቀላሉ ተቀባይነት የነበረው በመሆኑ፥ ኤርምያስ ራሱ እንደ ሐሰተኛ ነቢይ ተቆጥሮ ነበር፤ መልእክቱንም የሚሰማው አልነበረም።

12ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሐሰተኞች ነቢያት አሉን? መልስህን አብራራ። ለ) እነዚህ ሐሰተኞች ነቢያት የሚሠሩት እንዴት ነው? ሐ) መልእክታቸው በብዙ ሰዎች ዘንድ በቀላሉ ተቀባይነት የሚያገኘው ለምንድን ነው? መ) የእነዚህ ሐሰተኞች ነቢያት መልእክት የሚያስከትለውን መዘዝ ለመገደብ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ማድረግ ይችላሉ?

4. ኤርምያስ የባቢሎን ምርኮ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ በትክክል ተንብዮ ነበር፤ ይህም 70 ዓመታት ነበር (ኤርምያስ 29:10)። (70ውን የምርኮ ዓመታት በሚመለከት ቀደም ሲል ያሰፈርነውን በሁለት የተለያዩ መንገዶች የተሰጠ ማስታወሻ ተመልከት።) ባለመታዘዛቸው ምክንያት እግዚአብሔር ሕዝቡን

ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት አልፈለገም። በከፍተኛ ደረጃ የቀጣቸው ቢሆንም እንኳ ከቅጣቱ ጊዜ በኋላ ግን የምሕረትና የይቅርታ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደገዛ ምድራቸው ለመመልስ ተስፋ ሰጠ።

ኤርምያስ እስራኤል የምትመለስበትንና አሕዛብ በእግዚአብሔር የሚሸነፉበትን፥ እንዲሁም አይሁድ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በመፈጸም የሚኖሩበትን የመጨረሻ ዘመን አሻግሮ በመመልከት ተናግሯል። አይሁድ እስከ አሁን ድረስ በብዙ መንገድ በእግዚአብሔር ቅጣት ሥር ናቸው። ከአይሁድ ብዙዎች ወደ አገራቸው የተመለሱ ቢሆንም፥ ሌሎች እጅግ ብዙዎች ደግሞ በአሕዛብ መካከል ተበትነው ይገኛሉ። ይሁን እንጂ አንድ ቀን እግዚአብሔር እስራኤልን ዳግም በማነጹ እዛው በአሕዛብና በአይሁድ ላይ ይነግሣል።

13ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ኤርምያስ 31:31-34 አንብብ። በአዲሱ ቃል ኪዳን ውስጥ የተካተቱ ተስፋዎች ምንድን ናቸው? ለ) አዲሱ ቃል ኪዳን ከቀድሞው ቃል ኪዳን የሚለየው እንዴት ነው?

5. ኤርምያስ አዲስ ኪዳን የተመሠረተበትን አዲስ ቃል ኪዳን ያስተዋውቀናል። አዲሱንና የብሉይ ቃል ኪዳንን ብናወዳድር አንዳንድ ዐበይት ልዩነቶችን እንመለከታለን። ብሉይ ቃል ኪዳን የተመሠረተው በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ባለ የጋራ ስምምነት ላይ ነው። ቃል ኪዳኑ የተፈጸመው በስምምነት መልክ ሲሆን፥ እንዲታዘዙት እግዚአብሔር ያስቀመጠው ቅድመ ሁኔታ ነበር። ለሕጉ በሚሰጡት ምላሽ መሠረት በረከትና መርገም ይከተላቸው ነበር። ይሁን እንጂ አዲስ ኪዳን በስምምነት መልክ አልነበረም። ይልቁንም እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠው ተስፋ ነበር። እግዚአብሔር በሕይወታቸው ውስጥ እንዲሠራ ሕጉ በድንጋይ ጽላት ላይ ሳይሆን፥ በሰዎች ልብ ውስጥ መጻፍ ነበረበት። ይህም ሕጉን የበለጠ እንዲያውቁትና እንዲታዘዙት የሚያደርግ ነው።

ነገር ግን አዲሱ ቃል ኪዳን በብዙ መንገድ ሙሉ በሙሉ አዲስ አልነበረም። ሕግን (ኤርምያስ 31:33) የፓልስጢናን ምድር (ኤርምያስ 32:36-44) እንዲሁም የዳዊትን ሥርወ- መንግሥት (ኤርምያስ 33:15-26) ይጨምር ነበር። ይህም ማለት አዲሱ ቃል ኪዳን በሲና

ተራራ ላይ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር፥ ቀጥሎም ከዳዊት ጋር ያደረጋቸው የሁለት ቃል ኪዳናች ቅጥያ ነው ማለት ነው። በቀድሞውና በአዲሱ ቃል ኪዳን መካከል ያለው ትልቅ ልዩነት፡- በአሮጌው ቃል ኪዳን ውስጥ ከግብ ለማድረስ ፈጽሞ የማይቻለውን ጉዳይ በአዲሱ ቃል ኪዳን ውስጥ ግን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምክንያት የእግዚአብሔርን ሕግጋት ለመፈጸም መቻሉ ነው። ሁኔታዎቹ ከግቡ የሚደርሱት መንፈስ ቅዱስ ትክክለኞች የሆኑትን የእግዚአብሔር መመዘኛዎች ለመፈጸም የሚያስችል ኃይል ስለሚሰጥ ነው።

14ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ክርስቲያን ከሆንክ ጀምሮ ሕይወትህ እንዴት ነው የተለወጠው? ለ) ቅዱስ በሕይወትህ እንድትቀደስና የእግዚአብሔርን ሕግ ለመፈጸም እንድትችል መንፈስ ቅዱስ ሊረዳህ በመሥራት ላይ ያለው እንዴት ነው?

ትንቢተ ኤርምያስ ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ግንኙነት

ትንቢተ ኤርምያስ እንደ ትንቢተ ኢሳይያስ ከአዲስ ኪዳን ጋር በቅርብ የተያያዘ አይደለም። ትንቢተ ኤርምያስ ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው የቅርብ ግንኙነት ከቀድሞው ቃል ኪዳን የበለጠና የተሻለ አዲስ ቃል ኪዳን እንደሚመጣ ማመልከቱ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ያንን አዲስ ኪዳን አስተዋወቀ። ዛሬም እኛ ሁላችን በኢየሱስ ክርስቶስ በምናምንበት ጊዜ በዚያ ቃል ኪዳን ውስጥ እንጠቃለላለን።

አንዳንድ ምሁራን በኤርምያስና በኢየሱስ ክርስቶስ መካከል ብዙ ተመሳሳይነት መኖሩን ይናገራሉ። ሁለቱም አላገቡም፤ በወገናቸው ተንቀዋል፤ አገራቸውን አሳልፈው እንደሰጡ ተቈጥረው ተከሰዋል፤ በዘመናቸው ከነበሩት የሃይማኖትና የፖለቲካ መሪዎች ተቃውሞ ደርሶባቸዋል፤ ስለ ኢየሩሳሌም ንስሐ አለመግባትና ጥፋት አልቅሰዋል፤ ደግሞም በዓለም አመለካከት ያልተሳካላቸውና ጥቂት ተከታዮች የነበሯቸው ነበሩ።

2ኛ ቀን፡- ኤርምያስ 1-6

15ኛ ጥያቄ፥ ሀ) አንተ ባለህበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ ሰው መሪ የሚሆነው እንዴት ነው? የሚመረጠውስ እንዴት ነው?

ለ) አንድ ሰው የቤተ ክርስቲያን መጋቢ፥ ሽማግሌ ወይም ወንጌላዊ ለመሆን ሊኖሩት የሚገቡ የተለያዩ መመዘኛዎችን ዘርዝር።

አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሊኖረው ከሚገባ እጅግ ጠቃሚ ነገሮች አንዱ፡- የሚሠራው ሥራ እግዚአብሔር ሊያደርገው የሚፈልገው ነገር ለመሆኑ ማረጋገጥ አለበት። ይህን ማረጋገጫ ብዙ ጊዜ «የእግዚአብሔር ጥሪ» ብለን እንጠራዋለን። የቤተ ክርስቲያን መሪ የሚሠራው ሥራ እግዚአብሔር እንዲሠራ የሚፈልገው ጉዳይ መሆኑን፥ እግዚአብሔር በሰጠው ስጦታ እንደሚሠራና ሥራውንም የሚያከናውነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆኑን ማወቁ አስፈላጊ ነው። የሚያሳዝነው ግን ከመሪዎቻችን መካከል አብዛኛዎቹ ለመምራት በእግዚአብሔር ስለ መጠራታቸው ምንም የሚሰማቸው ነገር የለም። ለመሪነት የምትሾማቸው ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች ነው የሚያስቡት። በቤተ ክርስቲያን አመለካከት የመሪነት ብቃት ዋና መመዘኛ ሆኖ የሚቀርበው ሰውዬው ከትክክለኛ ትውልድ መምጣቱ፥ ከፍተኛ ትምህርት ያለው መሆኑ ወይም መሪ ለመሆን ያለው ትክክለኛ ማኅበራዊ ከበሬታ ነው። አንዳንድ ወጣቶች ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክብር ለማግኘት ወይም ሥራ ለመቀጠር የሚያስችል ስለሆነ መሪ ለመሆን ይፈልጋሉ።

አንድ መሪ የሚያደርገው ነገር እግዚአብሔር እንዲያደርገው የመረጠውን ተግባር ስለመሆኑ በጥልቀት የማይሰማው ከሆነ በአመራሩ ላይ ወዲያውኑ ችግሮች ይፈጠራሉ። በስግብግብነትና በራስ ወዳድነት ሀብትና ክብርን ለማካበት ሲል ይመራል። አንድ የተሻለ ሥራ በተሻለ ክፍያ በሚያገኝበት ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የአመራር ተግባር ይተዋል። አንድ ሰው እግዚአብሔር እንደጠራው ይህ ውስጣዊ ግንዛቤ ከሌለው፥ በስደት ጊዜ ጸንቶ ከመቆም፥ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚመጣውን አብዛኛውን ስደት ከመቀበልና አመራሩን ከመቀጠል ይልቅ የመሪነት ሥራውን ይተዋል።

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን የነበሩትን ነቢያት ለነቢይነት አገልግሎት የጠራቸው ግልጽ በሆነ ሁኔታ ነበር። እነርሱ መርጠው የገቡበት አልነበረም። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ነቢያትን ለመጥራት ትልልቅ ራእዮችን ይሰጥ ነበር (ለምሳሌ፡- ኢሳይያስ፥ ሕዝቅኤል)። ብዙውን ጊዜ

ግን የነቢያት ጥሪ ቀላል ነበር። እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን ሰዎች ለመጥራት የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀም ነበር። ዋናው ነገር እግዚአብሔር አንድን ሰው መጥራቱ ሳይሆን፥ ቤተ ክርስቲያንና ሰውዬው ራሱ፥ እግዚአብሔር ለዚያ አገልግሎት እንደጠራው መረዳታቸው ነው።

16ኛ ጥያቄ፥ ሀ) አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ሳይጠራቸው ወይም ስጦታ ሳይኖራቸው በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ በሚቀመጡበት ጊዜ ምን ዓይነት ችግሮች ተፈጥረው አይተሃል? ለ) ቤተ ክርስቲያንህ የተሻሉ መሪዎችን ለመምረጥ ምን ማድረግ የምትችል ይመስልሃል?

ኤርምያስ የአገልግሎት ጥሪውን የተቀበለው በወጣትነቱ ነው፤ ይሁንና በጥሪው ለ40 ዓመታት አገልግሎት ዘመኑ ተመርቶበታል፤ የደረሰበትንም ስደት እንዲቋቋም ረድቶታል።

17ኛ ጥያቄ፥ ከእግዚአብሔር ጥሪ አለህን? ከእግዚአብሔር ጥሪ አለኝ ካልክ፥ አንድ የተለየ ነገር ታደርግ ዘንድ እግዚአብሔር እንደ ጠራህ የተረዳህበትን መንገድ ግለጽ።
18ኛ ጥያቄ፥ ኤርምያስ 1-6 አንብብ። ሀ) የኤርምያስን ጥሪ ግለጽ። ለ) በኤርምያስ ምዕራፍ 1 የምትመለከታቸው ሁለት ራእዮች ምን ይመስሉሃል? ሐ) እስራኤላውያን በጥፋተኛነት የተከሰሱባቸውን የተለያዩ ኃጢአቶች ዘርዝር። መ) በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ተለይተው የተጠቀሱት የመሪዎች ኃጢአቶች ምንድን ናቸው?

1. የኤርምያስ ጥሪ (ኤር. 1)

ኤርምያስ እግዚአብሔር እንደጠራው ያውቅ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ እግዚአብሔር ኤርምያስን ለነቢይነት የመረጠው ገና በማኅፀን ሳለ መሆኑን ነግሮት ነበር። ኤርምያስ እግዚአብሔር በጠራው ጊዜ ገና ወጣት ስለነበረ ለመሪነት እንደማይበቃ አስቦ ነበር፤ እግዚአብሔር ግን እኔ ከአንተ ጋር ነኝ በማለት፥ እድሜ ምንም ለውጥ እንደማያመጣ እንደገና አረጋገጠለት። ኃይል የሚመጣው ከኤርምያስ እድሜ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል ከመናገሩ ነበር። የመንግሥታትን መደምሰስ የመተንበይ ችሎታ ለኤርምያስ የሰጠው ያ የእግዚአብሔር ቃል ነበር።

በኃጢአታቸው ምክንያት በይሁዳ ሕዝብ ላይ ፍርድ የሚመጣበት ጊዜ መኖሩን ገና ከጅምሩ እግዚአብሔር ለኤርምያስ ነግሮት ነበር። እንዲሁም የሰው ተቃውሞ የሚገጥመው ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር እንጂ ሰውን መፍራት እንደሌለበት ኤርምያስን አስጠንቅቆት ነበር።

19ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ብዙውን ጊዜ መሪዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰውን የሚፈሩባቸውን መንገዶች ግለጽ። ለ) ይህ ነገር በአንተ ሕይወት የደረሰው እንዴት ነበር?

እግዚአብሔር ለኤርምያስ ለመልእክቱ ምልክት የሚሆኑት ሁለት ራእዮች ሰጥቶት ነበር፤ እነርሱም፦

ሀ. ስለ ለውዝ ዛፍ በትር ያየው፦ በዕብራይስጥ የለውዝ በትርና «መጠበቅ» የሚሉት ቃላት አንድ ዓይነት ይመስላሉ። የዚህ ራእይ ትርጉም እግዚአብሔር የይሁዳን ሕዝብ ይጠብቃል፤ እርሱ አልተኛም ማለት ነው። እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ፍርድን ለማምጣት ቀርቦ ነበርና እግዚአብሔር እንደተናገረው ይፈጸም ዘንድ ቃሉ ይጠብቃል ማለት ነው።

ለ. በሰሜን አቅጣጫ ስላየው የሚፈላ ድስት ራእይ፦ ይህ ራእይ የሚያመለክተው በባቢሎን አማካይነት ስለሚመጣው የሰሜን ሠራዊት ጦርነት ነበር። እግዚአብሔር ይሁዳን ያጠቁ ዘንድ አሕዛብን እያንቀሳቀሰ ነበር። እግዚአብሔር በወሰነ ጊዜ፥ የእግዚአብሔር ፍርድ የሆነው ድስት በኃጢአታቸው ምክንያት የይሁዳን ሕዝብ ለመቅጣት ይፈስሳል።

2. የኤርምያስ የመጀመሪያ መልእክት፦ የይሁዳ ሕዝብ እምነት ማጣት (ኤርምያስ 2፡1-3፡5)

የመረጣቸውን-እግዚአብሔርን ያለ አንዳች ምክንያት እንደተዉት ኤርምያስ ለሕዝቡ ነገራቸው። በሞኝነታቸው ሌሎችን የድንጋይና የእንጨት አማልክት በመምረጥ የጣዖት አምልኮ ያዘወትሩ ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ ፍርድን ለማምጣት ወሰነ።

3. የኤርምያስ ሁለተኛ መልእክት፦ ተመለሱ ወይም የእግዚአብሔርን ፍርድ ተቀበሉ (ኤርምያስ 3፡6-6፡30)

ይሁዳም ልክ እንደ እስራኤል ስለሆነች እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ ተመሳሳይ ፍርድ ሊያመጣ ተዘጋጅቶ ነበር። ይሁን እንጂ ይሁዳ ለባለዋ እንዳልታመነች ሚስት ለእግዚአብሔር ያላትን ታማኝነት የተወች ቢሆንም፥ ሕዝቡ ንስሐ ቢገቡና መንገዳቸውን ቢለውጡ እግዚአብሔር ይሁዳን ይቅር ለማለት አሁንም ፈቃደኛ ነበር። ቢመለሱና መንገዳቸውን ቢለውጡ፥ እግዚአብሔር ተገቢ የሆኑ እረኞችን (መሪዎች) ይሰጣቸዋል። ኢየሩሳሌምና ይሁዳም ለእግዚአብሔር ክብርን ያመጣሉ። ንስሐ ካልገቡና ካልተመለሱ ግን ምድሪቱን ሙሉ በሙሉ የሚደመስስ ኃይል ከሰሜን ይመጣል።

20ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከእነዚህ የኤርምያስ መጽሐፍ ምዕራፎች ምን ማስጠንቀቂያዎችን መውሰድ እንችላለን? ለ) ቤተ ክርስቲያንህን ስለ ኃጢአትና ኃጢአት ስለሚያስከትላቸው ነገሮች፥ እንዲሁም ስለ ንስሐ አስፈላጊነት ለማስተማር እነዚህን ምዕራፎች እንዴት ትጠቀምባቸዋለህ?

3ኛ ቀን፡- ኤርምያስ 7-17

በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚመጣው ከፍተኛ አደጋ ስደት አይደለም። የሐሰት ትምህርትም አይደለም። ትልቁ አደጋ ግን ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖትን ቅርጽ ወይም ሥርዓታዊ አምልኮ ብቻ ይዛ መጓዟን፥ መቀበሏንና የሰዎችን ሕይወት የሚለውጥና በሰዎች አኗኗር ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ሃይማኖት አለመኖሩ ነው። በኤርምያስ ዘመን የነበሩ አይሁድ ወደ ቤተ መቅደስ እየሄዱ ማምለካቸውን አልተዉም ነበር። ለእግዚአብሔር የእንስሳ መሥዋዕት ማቅረባቸውን አልተዉም ነበር፤ ነገር ግን ይህ በየጊዜው የሚፈጸሙት ሥርዓት ብቻ ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት አልነበራቸውም። ሕይወታቸው እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ የሚመራ አልነበረም፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አምልኮአቸውን ለመቀበል አልፈለገም፤ በምትኩ ግን ፍርድ እንደሚያመጣባቸው ተናገረ።

21ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህ ነገር በቤተ ክርስቲያንህ ወይም በሌላ ቤተ ክርስቲያን ሲፈጸም ያየኸው እንዴት ነው? አንዳንድ ማስረጃዎች ስጥ። ለ) ይህ በግል ሕይወትህ ሊፈጸም የሚችለው እንዴት ነው? ሐ) አምልኮህ እውነተኛና በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ልታደርጋቸው የምትችላቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? መ) ይህ ነገር በቤተ ክርስቲያንህ አባላት ላይ እንዳይፈጸም ለማድረግ አንተ ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ማድረግ ትችላላችሁ?
22ኛ ጥያቄ፥ ኤርምያስ 7-17 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር የአይሁዶችን አምልኮ ያልተቀበለው ለምንድን ነው? ለ) በዚህ ክፍል ውስጥ የታዩትን የይሁዳ ኃጢአቶች ዘርዝር። ሐ) በዚህ ስፍራ ስለ ይሁዳ መሪዎች የተነገረው ምንድን ነው? መ) ኤርምያስ መንፈሳዊ እውነቶችን ለመግለጥ የተጠቀመባቸውን ምልክቶች ዘርዝር።

እነዚህ ምዕራፎች በሚጻፉበት ጊዜ፥ ኢዮስያስ የአይሁድን ሃይማኖት ለማደስ ፈልጎ እንደነበር አስታውስ። ተግባራቸውን ለተወሰኑ ጊዜያት ለመቀየር ችሎ ነበር፤ የሕዝቡ ልብ ግን አልተለወጠም ነበር። ኢዮስያስ ከሞተ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ሕዝቡ ወደ ሐሰተኛ ሃይማኖቱ ተመለሰ።

1. የኤርምያስ ሦስተኛ መልእክት ስለ አይሁድ አምልኮ መበላሸት የሚናገር ነበር (ኤርምያስ 7፡1-10፡25)።

አይሁድ የአምልኮ ሥርዓት እየፈጸሙ ቢመላለሱም እንኳ እግዚአብሔር ደስተኛ አልነበረም። እንደ ብዙዎቻችን ሁሉ በአምልኮ የሚያደርጉትን ነገር በሕይወታቸው ከሚለማመዱት ነገር ለይተውት ነበር። እግዚአብሔር ከአምልኮ ሕይወት ይልቅ በአምልኮ ተግባራት ላይ የበለጠ እንደሚያተኩር ይመስላቸው ነበር፤ ስለዚህ ሕይወታቸው እግዚአብሔርን የሚያስከብር እንዲሆን ምንም ጥረት አያደርጉም ነበር። ከሌሎች ጋር በቅድስናና በፍትሕ አይኖሩም ነበር። የዚህ ዓይነቱ አምልኮ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ የሌለው ከንቱ ነበር። አይሁድ የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነው ቤተ መቅደስ በመካከላቸው ስለነበር ኤርምያስ የሚናገረው የትንቢት ፍርድ ሊፈጸም ወይም ሊደርስባቸው እንደማይችል አድርገው ያስቡ ነበር፤ ስለዚህ ስለ መልእክቱ ይጠራጠሩ ነበር። ኤርምያስ በመጽሐፉ መሳፍንት ውስጥ እንደተጻፈው፥ በዔሊ ዘመን

የመገናኛው ድንኳን እንዲደመሰስና ታቦቱ እንዲማረክ እግዚአብሔር እንዴት እንደፈቀደ ማስታወስ ነበረበት (1ኛ ሳሙኤል 4)።

23ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ይፈርስና ይጠፋ ዘንድ እንደማይፈቅድ በሚያስቡ አንዳንድ ክርስቲያኖች ዘንድ ይህ ተመሳሳይ አመለካከት የሚታየው እንዴት ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ስላለ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን በኃጢአት ምክንያት አይቀጣም ለሚሉ ክርስቲያኖች እንዴት መልስ ትሰጣለህ?

የይሁዳ ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስና እርሱንም ለመታዘዝ በተደጋጋሚ እምቢ አሉ። ሐሰተኞች አማልክትን የማምለክ ተግባራቸው የበለጠ ግልጽ እየሆነ መጣ። ፍርድ የሚቀበሉበትን ጊዜ ወሰነ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ኤርምያስን ለሕዝቡ ደኅንነት ወይም ከጥፋት ነፃ መውጣት የሚያደርገውን ጸሎት እንዲያቆም ነገረው። ኤርምያስ ባቢሎናውያን ይሁዳን በሚወጉበት ጊዜ ስለሚመጣው ታላቅ ጥፋት ተነበየ።

ኤርምያስ ከተመኛቸው ነገሮች አንዱ፡- የተቀረጹ ምስሎችን ማምለክ ምን ያህል የሞኝነት ተግባር እንደሆነ ማስተማር ነበር። የተቀረጹ ምስሎች ሰዎች ከሚያገኟቸው ከማናቸውም ዓይነት ቁሳቁሶች የሠሯቸው ነበሩ፤ ነገር ግን ምንም ኃይል አልነበራቸውም። ከነዚህ ጋር ሲነጻጸር፥ የማይታየው አምላክ እጅግ ታላቅ ኃይል ነበረው። እርሱ ምድርን የፈጠረ ዘላለማዊ ንጉሥ ነው። ስለዚህ ኤርምያስ የተከተሉትን የሞኝነት መንገድ እንዲመለከቱና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ እስራኤላውያንን ያሳስባቸዋል። እነርሱ ግን በሞኝነታቸው ገፉበት፤ የእግዚአብሔርንም ፍርድ በራሳቸው ላይ አመጡ።

እግዚአብሔር በአብዛኛው ማንን ጥፋተኛ እንደሚያደርግ አስተውል። ለአብዛኛው ጥፋት ተጠያቂ ያደረጋቸው የይሁዳ የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎች የሆኑ እረኞችን ነበር። ከእግዚአብሔር ምሪትን ስለማይጠይቁ ምናምንቴዎች ነበሩ። የመጨረሻው ውጤት መንጋው በሙሉ ማለትም የእስራኤላውያን መበታተንና መጥፋት ነው።

24ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ መጥፋት የእስራኤልን ሕዝብ መሪዎች ዋና ተጠያቂዎች ያደረገው ለምን ይመስልሃል? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለሆንን ለእኛ ምን ማስጠንቀቂያ ይሆነናል? ሐ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተገቢ ያልሆነ አመራር በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ጉዳት ሲያስከትል ያየኸው እንዴት ነው?

2. የኤርምያስ አራተኛ መልእክት ይሁዳ ከእግዚአብሔር ጋር የገባችውን ቃል ኪዳን ስለ ማፍረሷ የሚናገር ነው (ኤርምያስ 11፡1-12፡17)።

እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር በሲና ተራራ ላይ የገባውን ቃል ኪዳን የማፍረሳቸው ክስ በብሉይ ኪዳን ነቢያት ልብ ውስጥ መቀመጡ የሚታወስ ነው፤ ስለዚህ ነቢያት ብዙውን ጊዜ በቃል ኪዳኑ ውስጥ የተገለጹት እርግማን መድረሳቸውን ያመለክቱ ነበር። ቃል ኪዳኑን ስላፈረሱ እርግማኑን መጋፈጥ እንደነበረባቸው ኤርምያስ ለሕዝቡ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአል። እንደገና ኤርምያስ ለሕዝቡ መጸለይ እንደማያስፈልገው ተነግሮት ነበር፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር መልስ አይሰጥም ነበርና ነው።

25ኛ ጥያቄ፥ እግዚአብሔር ስለማይመልስልን ዛሬ ልንጸልያቸው የማይገባን ጸሎቶች አሉን? አንዳንድ ምሳሌዎችን ዘርዝር።

ኤርምያስ የፍርድ መልእክትን በግልጽ በማወጁ፥ ከሕዝቡ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠመው። የገዛ ራሱ ነገድና ከትውልድ አገሩ የሆኑ ሰዎች ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር (ኤርምያስ 11፡18-23)።

ኤርምያስ፥ የይሁዳ ሕዝብ ያዘወትሩት የነበረውን ግልጽ የሆነ ክፉ ድርጊት በመመልከት፥ እግዚአብሔር አስቀድሞ የተናገረውን ፍርድ ለምን እንዳላመጣባቸው ይጠይቃል። ክፉዎች የሚከናወንላቸው እስከ መቼ ነው? እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደተዋቸውና ያለ እርሱ ጥበቃም ጥፋቱ እንደማይቀር ለኤርምያስ ነገረው።

3. የኤርምያስ አምስተኛ መልእክት ለምንም የማይረባ የወገብ መታጠቂያና በተቀደደ የወይን አቁማዳ ምልክትነት የተገለጠ ነበር (ኤርምያስ 13)።

እግዚአብሔር ሕዝቡ የጥፋት መልእክት እንዲሰሙ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፥ ለዚያ ጥፋት የሚታይ ምልክት አድርጎ ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ኤርምያስን ይሁዳ እንዴት ዋጋ እንዳጣች ለማሳየት፥ ሁለት ምልክቶችን እንዲያሳይ ኤርምያስን ጠየቀው። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ኤርምያስን ከተልባ እግር የተሠራች ካህናት የሚታጠቋት ዓይነት መታጠቂያ እንዲገዛና እንዲታጠቅ አዘዘው። ይህች መታጠቂያ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር የተቀደሱ የእግዚአብሔር ካህናት መሆን እንደነበረባቸው የምታስታውሳቸው ነበር (ዘጸአት 19፡6 ተመልከት)። ይህችን መታጠቂያ ወደ ጴራክ ወስዶ እንዲሸሽጋት ተነገረው። ይህች ስፍራ በመቶ የሚቈጠሩ ኪሎ ሜትሮች ርቃ ከኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ የምትገኝ ነበረች። ይህ የአሦራውያንና የባቢሎናውያን ክፉ ተጽዕኖ የሚመጣበትን አቅጣጫ የሚያሳይ ነበር። ከብዙ ቀናት በኋላ ኤርምያስ የተበላሸችውን መታጠቂያ ለሕዝቡ እንዲያሳይ ተነገረው። ይህም የእግዚአብሔር ሕዝብ በምድራቸው እያሉ በአሕዛብ ተፅዕኖ መበላሸታቸውን ብቻ ሳይሆን ወደፊትም በምርኮ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ እንደሚበላሹ የሚያሳይ ነበር። በዚህ ጊዜ ለእግዚአብሔር ያላቸው ጠቀሜታ ያከትማል።

ሁለተኛው ምልክት በወይን የተሞላ አቍማዳ ነበር። በጥንት ዘመን በጎብረተሰቡ ዘንድ ከሚታወቁ ክፉ ነገሮች መካከል አንዱ ሰካራምነት ነበር። ብዙ መሪዎች ሰካራሞች በመሆናቸው ይመኩ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሕዝቡን በተለይ መሪዎችን ለየት ባለ መንገድ ሰካራሞች ያደርጋቸዋል። በቍጣው መዓት እንዲሰክሩ ሲያደርግ በእነርሱ መዘጋጀቱን ያሳያል። ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነው ይህ ፍርድ በከፊል የጠላት ወረራ በሚመጣበት ጊዜ፥ ሕዝቡ የሰከሩ በመምሰል፥ ጠላቶቻቸውንና ወዳጆቻቸውን ለይተው መናገር እስከማይችሉ መድረሳቸው ነው።።

ከዚያም ኤርምያስ ግልጽ በሆነ መንገድ ስለሚመጣው ምርኮ ተነበየ። ንጉሡና የንግሥቲቱም እናት ሳይቀሩ ከሰሜን በሚመጡት በባቢሎናውያን እንደሚማረኩ ተናገረ።

4. የኤርምያስ ስድስተኛ መልእክት ስለሚመጣው ድርቅ የተነገረ ነበር (ኤርምያስ 14፡1-15፡21)።

በትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ በሕዝቡ ላይ ስለሚደርሱ ሦስት ዐበይት የጥፋት ምንጮች በተደጋጋሚ እናነባለን። በዝናብ ዕጥረት ምክንያት የተከሠተ ድርቅ ነበር። ምግብ ባለመኖሩ ምክንያት ደግሞ ራብ ነበር። ራብ የድርቅ ወይም ሰብል ሁሉ የሚደመሰስበትና የእርሻ ሥራ የሚቋምበት የጦርነትም ውጤት ሊሆን ይችላል። በመጨረሻ ሰይፍ ነበር፤ ይኸውም ሰይፍ በጠላት ውጊያ የሚመጣ ጥፋት ነበር። እግዚአብሔር ለኤርምያስ የፍርዱ ቀን ስለደረሰ፥ ስለ ሕዝቡ ነፃ መውጣት መጸለይ እንደሌለበት ለሦስተኛ ጊዜ ይነግረዋል። በዚያን ወቅት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ታላላቅ የጸሎት ሰዎች በመሆናቸው የሚታወቁት ሁለቱ ሰዎች ማለትም እስራኤላውያን በሲና ተራራ ፈጽመው እንዳይጠፉ የማለደው ሙሴና ሕዝቡ ንጉሥ እንዲነግሥላቸው በጠየቁ ጊዜ ሊጸልይላቸው ቃል የገባው ሳሙኤል እንኳ ለሕዝቡ ቢማልዱ፥ እግዚአብሔር አይሰማቸውም ነበር።

ኤርምያስ ሊመጣ ስላለው ጥፋት የተሰማውን ጎዘን ይገልጻል። ዓይኖቹ እንባ አዝለው፥ ልቡም ተሰብሮ ነበር፤ ይህም ሆኖ በእግዚአብሔር ምሕረት ይተማመን ነበር። እንዲሁም ኤርምያስ ሕዝቡ በመልእክቱ ላይ የሚሰነዘሩትን ተቃውሞ መቀበል ጀምሮ ነበር። እግዚአብሔር ግን ሊያጠፋት ቢፈልጉም እንኳ እርሱ ስለሚታደገው ሊያሸንፉት እንደማይችሉ በመናገር አበረታታው።

5. የኤርምያስ ሰባተኛ መልእክት፡- ሳያገቡ ስለመኖር ተምሳሌትና ስለይሁዳ ጥፋት ነበር (ኤርምያስ 16-17)።

እግዚአብሔር ሊመጣ ስላለው ነገር ለመናገር የኤርምያስን ሕይወት ቋሚ ምልክት አድርጎት ነበር። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሚስት እንዳያገባ ወይም ልጆች እንዳይወልድ ነገረው። በአይሁድ ባህል አንጻር ማግባትና ልጅ መውለድ በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ስለነበር ለኤርምያስ ይህ ትልቅ ሸክም ነበር። አንድ አይሁዳዊ በሕይወቱ እንዳያጋጥሙት እጅግ ከሚሰጋባቸው ነገሮች ምንም ልጅ ከሌለው ስሙ ስለሚጠፋ (መታሰቢያ ስለማይኖረው) ልጅ እንዳያጣ ነበር፤ ነገር ግን ኤርምያስ ይህንን እጅግ ከባድ ትእዛዝ ፈጸመ። እግዚአብሔር ኤርምያስን ሚስት እንዳያገባ የከለከለው ለሕዝቡ በራሳቸው፥ በሚስቶቻቸውና በልጆቻቸው ላይ ሊመጣ ያለውን ጥፋት ያለማቋረጥ እንዲያስታውሳቸው ነበር።

እግዚአብሔር ለኤርምያስ የነገረው ሌላው ጉዳይ ደግሞ ሰዎች በሚሞቱበት ጊዜ እንዳያለቅስና እንዳያዝን ነበር፤ ምክንያቱም የሕዝቡ መሞት የእግዚአብሔር ፍርድ ስለነበር ኤርምያስ እግዚአብሔርን በመቃወም የቆሙ ሰዎች ሲፈረድባቸውና የሚገባቸውን ቅጣት ሲቀበሉ በማዘን በእግዚአብሔር ፍርድ ያለመስማማቱን ማሳየት ስላልነበረበት ነው።

እግዚአብሔር ኤርምያስን በሠርግ ወይም በሌላ የደስታ ጊዜያት እንዳይደሰት ነግሮት ነበር። ይህም በባቢሎን አማካይነት በይሁዳ ላይ ሊመጣ ያለውን የጥፋት ጎዘን በሕይወቱ የሚያሳይ ምልክት ነበር።

ፍርድ መምጣቱ የተረጋገጠ ቢሆንም እንኳ ፍርድን እንደሚያመጣ የተናገረ እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ መመለስም ተናግሮ ነበር። አንድ ቀን የእግዚአብሔር ሕዝብ ከተበተኑባቸው አገሮች ሁሉ ወደ አገራቸው ይሰበሰባሉ።

26ኛ ጥያቄ፥ ኤርምያስ 17፡5-8 አንብብ። ሀ) ብርታት ለማግኘት በሥጋ ላይ ልንታመን የምንችለው እንዴት እንደሆነ ምሳሌዎችን ጥቀስ። ለ) ስለ ችሎታችን ወይም ብቃታችን በእግዚአብሔር ላይ እንዴት መታመን እንደምንችል ምሳሌዎችን ጥቀስ። ሐ) ኤርምያስ በሰውና በእግዚአብሔር በሚታመን ሰው መካከል ስላለው ልዩነት የሚናገረው ምንድን ነው?

ኤርምያስ በተለይ በእግዚአብሔር አመለካከት ክፉ ስለሆነ አንድ ሌላ ኃጢአት ይገልጽልናል፤ ይህም እግዚአብሔር ስለ ሰንበት ወይም ቅዳሜ ዕረፍት የሰጠውን ትእዛዝ መጣስ ነበር። የእስራኤላውያን የሰንበት ዕረፍት ቅዳሜ ነበር። በብሉይ ኪዳን ከተሰጡ ዋና ዋና ትእዛዛት መካከል ሰንበትን መጠበቅ አንዱ ቢሆንም፥ እስራኤላውያን ግን ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ ይልቅ ሥጋዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎታቸውን አስቀድመው ነበር፤ ስለዚህ የሰንበትን ሕግን መጣስ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ትተው በራሳቸው መንገድ መሄዳቸውን ከሚያሳዩ ምልክቶች አንዱ ነበር።

27ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከእነዚህ ምዕራፎች የምንማራቸውን ትምህርቶች ዘርዝር። ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ኃጢአት፥ ስለ እግዚአብሔር ፍርድና እግዚአብሔር ከእኛ ስለሚፈልገው ነገር ምን እንማራለን? ለ) እነዚህ ቊጥሮች ከሚያስተምሯቸው ነገሮች መካከል ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የምንረሳቸው ወይም የማንሰብካቸው የትኞቹ ናቸው?

4ኛ ቀን፡- ኤርምያስ 18-25

እግዚአብሔር ከግለሰቦች ጋር እንደሚሠራ ሁሉ፥ በቡድን ከሰዎች ጋር ወይም ከአብያተ ክርስቲያናት ጋርም ይሠራል፤ በሁለቱም ረገድ የራሱ ዓላማዎች አሉ። በግለሰብ ደረጃ፥ ለሁላችንም ያለው ዓላማ ኢየሱስ ክርስቶስን እስክንመስል ድረስ እያንዳንዳችንን መቅረጽ ነው (2ኛ ቆሮንቶስ 3፡18)። በአብያተ ክርስቲያናት ደረጃ ደግሞ የእግዚአብሔር ፍላጎት ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቁ የሆነች ቅድስትና ንጽሕት ሙሽራ እንድትሆን ነው (2ኛ ቆሮንቶስ 11፡2)። በግለሰብ ወይም በአብያተ ክርስቲያናት ደረጃ፥ እግዚአብሔር በሕይወታችን በሚፈጽመው ሥራ፥ ኢየሱስ ክርስቶስን የመምሰሉን ሂደት በማፋጠን ረገድ ልንተባበር እንችላለን። ወይም ደግሞ ይህንን ለውጥ በሕይወታችን ልንቃወም እንችላለን፤ ይህ ሲሆን ግን እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ያደርገን ዘንድ ዋናውን ሥራ የሚሠራው እርሱ ይሆናል። ይህም እግዚአብሔር መልሶ እኛን ከመሥራቱ በፊት በሕይወታችን ውስጥ ብዙ ችግርና ሥቃይ ጥፋትም ይፈጸማል። እግዚአብሔር ለኤርምያስ ይህንን መመሪያ ለማስረዳት ሸክላ ሠሪን እንዲመለከት ያዘዋል። ሸክላ ሠሪው አንድ ማሰሮ ለመሥራት ሞክሮ ስለተበላሸበት ሙሉ ለሙሉ እንደገና አፍርሶ መሥራት ነበረበት። እግዚአብሔርም እንደዚሁ ይሁዳን ውብ አድርጎ ለመሥራት ፈልጎ ነበር፤ ይሁዳ ግን ፈቃደኛ ሳትሆን ቀረች፤ ስለዚህ በምርኮና በፍርድ እግዚአብሔር ይሁዳን አንድ ቀን እርሱ እንደሚፈልገው እስክትሆን ድረስ ሊሠራት ፈለገ።

28ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስን እስክትመስል ድረስ እግዚአብሔር በሕይወትህ የሚሠራባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) ከቤተ ክርስቲያንህ ቅድስትና የበለጠ ጠቃሚ እንድትሆን እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የሚሠራባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ሐ) ከዚህ መንፈሳዊ መመሪያ ልንወስዳቸው የሚገባን ማስጠንቀቂያዎች ምንድን ናቸው?

29ኛ ጥያቄ፥ ኤርምያስ 18-25 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር ክክፉ ሥራቸው የሚመለሱ ሕዝብ ምን ይሆናሉ አለ? ለ) ክፉ ሥራን የሚሠሩና ከእርሱ የማይመለሱ ሕዝብስ ምን ይሆናሉ? ሐ) በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላይ ምን ይመጣባቸዋል? መ) የተሰበረው ሸክላ ዕቃ የምን ምልክት ነው? ሠ) ጳስኮር በኤርምያስ ምን አደረገ? ረ) ኤርምያስ በእግዚአብሔር ላይ ያቀረበው ስሞታ ምን ነበር? ሰ) በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የተጠቀሱ ልዩ ልዩ ነገሥታትን ጥቀስ። ሸ) ስለ ዳዊት የዘር ግንድ የተነገረው ትንቢት ምንድን ነው? ቀ) ስለ ሐሰተኛ ነቢያት የተሰጠው ትንቢት ምንድን ነው? በ) ስለ ምርኮው ዘመን ርዝመት የተሰጠው ትንቢት ምንድን ነው?

---

1. ኤርምያስ በሸክላ ሠሪውና በተሰበረ ጠርሙስ ምልክትነት የሰጠው ስምንተኛ መልእክቱ (ኤርምያስ 18-20)

የሸክላ ሠሪነት ተግባር በኢትዮጵያውያን የተጠላ ቢሆንም በአይሁድ ዘንድ ግን የተናቀ አልነበረም። ይልቁንም የተከበረ ሙያ ነበር። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በሸክላ ሠሪ እየተመሰለ የቀረበው ለዚህ ነው። እግዚአብሔር ኤርምያስን ሂድና ሸክላ ሠሪውን ተመልከት አለው። ኤርምያስም ሸክላ ሠሪው አንድ የሸክላ ዕቃ በሚሠራበት ጊዜ ሲበላሽበት፥ የተበላሸውንም ዕቃ በማፈራረስ ከዚያው ሸክላ አዲስ ዕቃ ሲሠራ ተመለከተ። እግዚአብሔር ከዚህ ምልክት እስራኤላውያንን ያስተማራቸው ነገር፥ የመጀመሪያው የሸክላ ዕቃ የሆኑት በኃጢአት ምክንያት ቢበላሹ፥ እነርሱን አፍርሶ ሌላ የሸክላ ዕቃ ለመሥራት እንደሚችል ነበር። ይህ ትምህርት ሌሎችንም ሕዝቦች በሙሉ የሚመለከት ነበር። ከኃጢአቱ ንስሐ የሚገባ ማንኛውም ሕዝብ ይድናል፤ በክፉት ሥራው እየቀጠለ የሚሄድ ሕዝብ ሁሉ ግን ይጠፋል። ይሁዳ በክፉት ሥራው እየቀጠለ ከሚሄድ ሕዝብ መካከል የሚመደብ በመሆኑ፥ እግዚአብሔር ሊያጠፋው ተዘጋጅቶ ነበር።

ኤርምያስ የእስራኤልን ሕዝብ መጥፋት ለማመልከት ሌላ ምሳሌያዊ ድርጊት ተጠቅሞ ነበር። ኤርምያስ አንዳንድ የፖለቲካ መሪዎችን (ሽማግሌዎችን) እና ሃይማኖታዊ መሪዎችን (ካህናትን) ወደ ሄኖም ሸለቆ ይዞአቸው እንዲሄድ ተነገረው። የሄኖም ሸለቆ ከኢየሩሳሌም ቅጥር ክልል ውጭ የሚገኝ ስፍራ ነበር። በዚያ ስፍራ ለበአልና ለሌሎችም አማልክት ሰው እንደ መሥዋዕት ይቀርብላቸው ነበር። በዚያ ስፍራ እግዚአብሔር ኤርምያስን ገንቦ እንዲወስድና እንዲሰብር በመንገር፥ የይሁዳ ሕዝብም እንዲሁ እንደሚደመሰሱ አመለከተ። አይሁድ ልጆቻቸውን መሥዋዕት አድርገው ለጣዖት ወይም ለባዕድ አማልክት የሚያቀርቡበት ይህ ስፍራ ከባቢሎን ጋር በሚካሄድ ጦርነት በሚወድቁ ሰዎች ሬሳ ይሞላል። እንዲያውም ወላጆች ልጆቻቸውን እስኪበሉ የሚያደርስ የከፋ ራብ ይሆናል። በኢየሱስ ዘመን ይህ ሸለቆ ቆሻሻ የሚጣልበትና የሚቃጠልበት ሲሆን፥ የገሃነም ምሳሌ ሆኖ ነበር።

ኤርምያስ ይህን መልእክት ከተናገረ በኋላ ከካህናት አንዱ የሆነው ጳስኮር ኤርምያስን መታው። ለአንድ ምሽት በላይኛው በብንያም በር ባለው በእግር ግንድ ውስጥ አሳደረው። ይህም ኤርምያስ ከሕዝቡ በኩል ከሚደርሱበት የስደት ዓይነቶች አንዱ ነበር። ኤርምያስ በእግዚአብሔር ላይ በማጉረምረም፥ ባይወለድ ይሻለው እንደነበር ተናገረ። ዝም በማለት ከስደት ለማምለጥ በሞከረ ጊዜ ግን የእግዚአብሔር ቃል በውስጡ እያቃጠለው የባሰ ስደት ቢያስከትልበትም እንዲናገር ያስገድደው ነበር።

30ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የሌሎች ሰዎችን ፈጠና ቀልድ ወይም ነቀፋ በመፍራት የእግዚአብሔርን ቃል ያለመናገር ስሜት ተሰምቶህ ያውቃልን? ለ) አንድ ክርስቲያን ለኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ እንዲኖርና ያለማቋረጥ ወንጌልን ለሌሎች እንዲያካፍል የሚያደርገው ነገር ምን መሆን አለበት? ሐ) በኤርምያስ ላይ የደረሰው ነገር በተፈጸመ ጊዜ ብትኖር ኖሮ ለኤርምያስ ምን ምክር ትሰጠው ነበር?

2. የኤርምያስ ዘጠነኛ መልእክት የይሁዳን ነገሥታት የሚመለከት ነበር (ኤርምያስ 21፡1-23፡8)።

ኤርምያስ 21 የተፈጸመው ናቡከደነፆር በኢየሩሳሌም ላይ ጥቃት በፈጸመ ጊዜ ነበር። ንጉሥ ሴዴቅያስ፥ ኤርምያስ የሚለውን ለመስማት

በፈለገ ጊዜ፥ ባቢሎናውያን ወደ ኢየሩሳሌም ሊገቡ እንዳለና ንጉሥ ሴዴቅያስና ሕዝቡ እንደሚቀጡ ተናግሮ ነበር።

እነዚህ ምዕራፎች የተጻፉት ከዳዊት ዘር በርካታ ነገሥታት በነገሡበት ዘመን ነበር። ኤርምያስ ከዳዊት ዘር የሆኑትን ነገሥታት በጽድቅ ባለማስተዳደራቸውና እግዚአብሔር እንደፈለገው ባለመግዛታቸው ገሠጻቸው። እነዚህ ነገሥታት በራሳቸው ብርታትና ጥንካሬ ተማምነው ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ደግሞ በነገሥታቱ ላይ ለመፍረድ ተዘጋጅቶ ነበር።

ዳሩ ግን አንድ ቀን እግዚአብሔር ከዳዊት ዘር ጻድቅ ቍጥቋጥ ያስነሣል፤ «እግዚአብሔር ጽድቃችን» ተብሎም ይጠራል። እግዚአብሔርን የሚያከብር ዓይነት ንጉሥም ይሆናል። እስራኤልንና ይሁዳንም ነፃ ያወጣል። በእርግጥ ይህ ከዳዊት የዘር ሐረግ ስለሚወጣው የመጨረሻ ንጉሥ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረ ትንቢት ነው።

3. የኤርምያስ አሥረኛ መልእክት በይሁዳ ሐሰተኛ ነቢያት ላይ ያነጣጠረ ነበር (ኤርምያስ 23፡9-40)።

ኤርምያስ በየሄደበትና የእግዚአብሔርን እውነት በሰበከበት ስፍራ ሁሉ ከእግዚአብሔር ተልከናል እያሉ ሐሰትን የሚናገሩ የነበሩ በርካታ ሐሰተኞች ነቢያት ነበሩ። በእነዚህ ሐሰተኞች ነቢያት ምክንያት ሕዝቡ መንገዳቸውን እንዲቀይሩ የሚጠይቀውንና ተወዳጅ ያልነበረውን የኤርምያስን መልእክት ከመስማት ታቀቡ። የቃላቸው ሐሰተኛነት ብቻ ሳይሆን ተግባራቸውም ክፉ ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በሐሰተኞች ነቢያት ላይ ሊፈርድ ተዘጋጅቶ ነበር።

> 31ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ሐሰተኞች ነቢያት ዛሬ የሚሠሩት እንዴት ነው? ለ) ብዙ ክርስቲያኖችን ወደ ስሕተት የሚመሩት እንዴት ነው? ሐ) በእውነተኞችና በሐሰተኞች ነቢያት መካከል ያሉትን ልዩነቶች መነጋገር የምንችልባቸው ነጥቦች ምንድን ናቸው? መ) የሐሰተኞች ነቢያትን ተጽዕኖ ለመቋቋም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ማድረግ ይችላሉ?

4. የኤርምያስ አሥራ አንደኛ መልእክት የሁለት ቅርጫት በለስ ነበር (ኤርምያስ 24)።

ኤርምያስ ሁለት ቅርጫት ሙሉ በለስ ተመለከተ። ይህ ያመለከተው ሁለት ዓይነት የይሁዳ ሕዝብ መኖራቸውን ነበር። ለመብላት መልካም የሆኑ በለስ የሞሉበት ቅርጫት ወደ ምርኮ የሚወሰዱትን ጻድቃን የይሁዳ ሰዎችን ሲያመለክት፥ በምርኮ በሚሆኑበት ምድር እግዚአብሔር እንደሚጠብቃቸውና አንድ ቀን ወደ ገዛ ምድራቸው-ወደ ከነዓን እንደሚመልሳቸው የሚናገር ነበር።

ለመብላት መልካም ያልሆነ በለስ የሞሉበት ቅርጫት የሚወክለው በከነዓን ምድር የሚቀሩ ወይም ወደ ግብፅ የሚሸሹና እግዚአብሔርን የማይወዱ ሰዎችን ነበር። እግዚአብሔር ተስፋ በሰጣቸው ምድር እንዳይደሰቱ በሰይፍ፥ በራብ፥ በመቅሠፍትና በጥፋት ይፈርድባቸዋል።

5. የኤርምያስ አሥራ ሁለተኛ መልእክት ግዞትና ከምርኮ አገር ስለ መመለስ ነበር (ኤርምያስ 25)።

ይህ መልእክት የተሰጠው ኢየሩሳሌም በባቢሎን እጅ ለመውደቅ በተቃረበችበት በ605 ዓ.ዓ. ነበር።

ኤርምያስ ለአይሁድ የተናገረው እርሱን ስላልሰሙት ኢየሩሳሌም እንደምትጠፋና ሕዝቡም እንደሚማረኩ ነበር። በዚህ ስፍራ ግን የምርኮው ዘመን ለሰባ ዓመት ብቻ እንደሚሆንና ከዚያ በኋላ ምርኮው ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚመለስ በመናገር ለመጀመሪያ ጊዜ ሕዝቡን ያበረታታቸዋል።

የሰባ ዓመቱ ምርኮ የተጀመረበትን ጊዜ በሚመለከት ምሁራን የተለያየ አሳብ አላቸው። አንዳንዶች ይህ ቍጥር የምርኮውን አጠቃላይ ዘመን የሚወክል ቍጥር ነው ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ይህ ቍጥር ትክክለኛ የዓመታት መግለጫ ሆኖ ከ605-539 ዓ.ዓ. ያለውን ጊዜ ማለትም ኢየሩሳሌም ከተደመሰሰችበትና ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥ መግዛት ካቆመበት ጀምሮ አይሁድ እስከተመለሱበት ጊዜ ድረስ ያለውን የሚያመለክት ነው ሲሉ፥ ሌሎች ደግሞ ይህ 70 ዓመት የሚያመለክተው ቤተ መቅደሱ ከተደመሰሰበት ከ586 ዓ.ዓ. ጀምሮ እንደገና እስከተሠራበት እስከ 516 ዓ.ዓ. ድረስ ያለውን የአይሁድ የሃይማኖት በምርኮ ሥር የቆዩበት ጊዜ እንደሆነ ይናገራሉ።

32ኛ ጥያቄ፥ ዳንኤል 9 አንብብ። አይሁድ የሚመለሱበት ጊዜ እንደተቃረበ በተረዳ ጊዜ ዳንኤል ምን እያነበበ ነበር?

የእግዚአብሔር ፍርድ በአይሁድ ላይ ብቻ ሳይሆን በቀሩት አሕዛብም ላይ የሚደርስ ነበር። እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመቅጣት ለጊዜው በተጠቀመባቸው በባቢሎናውያን ላይ ይፈርዳል። እንዲሁም በይሁዳ አካባቢ በሚኖሩና ኢየሩሳሌምን ለማጥፋት በተባበሩ ሕዝቦች ሁሉ ላይ ይህ ፍርድ ይመጣል። አንድ ጽዋ ወይን አንድን ሰው እንደሚያሰክር ሁሉ የእግዚአብሔር የቍጣ ጽዋ ደግሞ በአሕዛብ ሁሉ ላይ ጥፋትን ያመጣል። የኤርምያስ የትንቢት ዓይን በቅርብ ጊዜ እነዚህ አሕዛብ አብዛኞቹ በባቢሎንና በሌሎችም አገሮች እንደሚጠፉ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ በሚነሡ ክፉ ሕዝቦችና መንግሥታት ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር የመጨረሻ ፍርድ የሚገለጽበትን የፍጻሜ ዘመን ጭምር ተመልክቶ ነበር።

33ኛ ጥያቄ፥ ሀ) መንግሥታትና ክፉዎች ሰዎች ሁሉ አንድ ቀን የእግዚአብሔርን ፍርድ እንደሚቀበሉ በሚያውቁበት ጊዜ ክርስቲያኖች በእምነታቸው ጸንተው እንዲራመዱ የሚያበረታታቸው እንዴት ነው? ለ) ክርስቲያኖች ወደ ዓለም እንዳይመለሱ ለማስጠንቀቅ እነዚህን ምዕራፎች እንዴት ልንጠቀምባቸው እንችላለን?

5ኛ ቀን፡ -

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የመወያያ ጥያቄዎችን ተመልከት።

ሳምንታዊው የስብሰባ ጊዜ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. የውይይት ጥያቄዎች

ሀ. 1) የኤርምያስን ባሕርይና አገልግሎት በአጭሩ ግለጽ። 2) ብዙውን ጊዜ ኤርምያስ እንደሚዋጣለት መሪ ዓይነት ባሕርይ የለውም

የምንለው በምን መንገድ ነው? 3) ኤርምያስ በእግዚአብሔር ዓይን የተዋጣለት መሪ የነበረው ለምንድን ነው? 4) ከኤርምያስ ሕይወት ስለ መሪነት ምን እንማራለን?

ለ. 1) በትንቢተ ኤርምያስ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ዐበይት እውነቶችን ከልስ። 2) እነዚህ ጠቃሚ የሚሆኑት ለምንድን ነው?

ሐ. 1) ከትንቢተ ኤርምያስ ስለ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ምን እንማራለን? 2) ቤተ ክርስቲያንህን የሚያውኩትን የተለያዩ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ወይም ትምህርቶች ጥቀስ። 3) እነዚህን ሐሰተኞች መሪዎች ለመቋቋም አንተና ሌሎች መሪዎች፥ በመሪነታችሁ ልታደርጉት የሚገባችሁ ነገር ምንድን ነው?

መ. ኤርምያስ 31፡31-34 አንብብ። 1) በአዲሱ ቃል ኪዳን ውስጥ የተሰጡትን የተለያዩ ተስፋዎች ዘርዝር። 2) እነዚህን ተስፋዎች በአሮጌው ቃል ኪዳን ውስጥ ከነበሩት ጋር አወዳድር። 3) አዲሱ ቃል ኪዳን የተፈጸመው በምን መንገድ ነው? ገና ሊፈጸም ያለውስ በምን መንገድ ነው?

ሠ. 1) እግዚአብሔር በይሁዳ መሪዎች ላይ ያቀረባቸው አንዳንድ ወቀሳዎች ምን ነበሩ? 2) እግዚአብሔር በይሁዳ መሪዎች ላይ እጅግ የከፋ ፍርድ ያመጣው ለምን ይመስልሃል? 3) ስለ ክርስቲያናዊ መሪነትና በእግዚአብሔር ዘንድ ስለ መጠየቅ ከኤርምያስ ምን እንማራለን?

5. ጸሎት።